# ምዕራፍ 6

## ዳግም ወደ አሜሪካ ከቤተሰብ ጋር

አዲስ አበባ ተግባረዕድ ት/ቤት ማስተማር በጀመርኩ በሁለተኛው አመት በድጋሜ የአስኮላርሺፕ እድል ተሰጠኝ፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሩሲያን በጎበኙበት ወቅት የሩሲያ መንግሥት ለኢትዮጵያ የሰጠው ስጦታ አንድ ሺህ ተማሪዎችን የሚያሰለጥን የቴክኒክ ት/ቤት ከሙሉ መማሪያ እቃ ጋር መገንባት ነበር፡፡ ይህንም ት/ቤት ባህር ዳር ላይ መገንባት ተጀምሮ ነበር፡፡ በዚህ ት/ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ከምእራብ አገሮች በተለይ ከአሜሪካ እንዳይሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ተደርሶ ስለነበር የኢትዮጵያ መንግሰት መምህራን ማዘጋጀት ነበረበት። ከተግባረዕድ ተመርቀን ለሁለት አመት ያህል ሰልጥነን በተግባረእድ ት/ቤት በማስተማር ላይ ያለን መምህራን በአዲሱ ት/ቤት ለማስተማር ብቁ ስላልሆንን ለእኛና ለሌሎችም ስኮላርሺፕ እንዲሰጥ ተወሰነ፡፡

የአሜሪካው ፖይንት ፎር ሖርሐ ግብር ለዚህ ሥራ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ሠራተኞች በሁለት አመት የባችለር ዲግሪ ሥልጠና ለመስጠት ነበር ዕቅዱ፡፡ ባለፈው ሥልጠና አብረን የነበርን ተማሪዎች በአሁኑ ዙርም ነበሩበት፡፡ ይህ እድል ሲሰጠኝ ግደይ አማኑኤልን ቅሪት ነበረች፤ ስኮላርሺፑ ሚስትና ልጅ ይዞ የሚያስኬድ አልነበረም፡፡ እቤት ስደርስ ለግደይ፡- አዲስ ስኮላርሺፕ እንዳገኘሁ ስነግራት፡-

"ታዲያ ምን አለ ሂዳ" ከምታገኛት የቻልከውን ትልክልናለህ፤ እኔም ሥራ አይዝና ከነልጄ ራስን ለመቻል እሞክራለሁ" አለቺኝ። እሺ ብዬ ተመዘግብሁ። ለወዳጅ ዘመድ እንደገና ለትምህርት ወደ አሜሪካ እንደምሄድ ተናገርሁ፤ ይህን





ከሰሙት ውስጥ ጥቂቶች ወዳጆቼ ግደይን ይዘሃት መሄድ አለብህ፤ በተለይ ሚሺነሪዎቹ ወዳጆቼ ይዘሃት ካልሄድህ መሄድ የለብህም አሉኝ፡፡ በነገሩ በጥልቀት አሰብኩበት። እኔም በሃሳቡ አመንኩበት ግደይን ይዤ ለመሄድም ቆርጬ ተነሳሁ፡፡

### የመጀመሪያ ልጃችን አማኑኤል

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ግደይ ከሳምንት በፊት ወዳጃችን (ሚዜአችን) ዶክተር ዮደር እንዲያዋልዳት ወደ ናዝሬት ኃ.ማ.ማ.መ. ሆስፒታል ሄዳለች፡፡ አንድ ቀን በጠዋት ሚስተር ሴንለኒንግ ወደ ቤቴ መጡ፤ ሳያቸው መደሰቴን ሲያዩ አይ ገና ነው፣ ገና ነው፤ ዶክተር ዮደር ግን መምጣት ያስፈልገዋል ብሎ ደውሏል አሉኝ። ሚስተር ሴንለኒንግ መጥተው ስለነገሩኝ አመሰግኜ ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ ጓደኛዬን አለፋ ገ/ጊዮርጊስ እንዲያስተምርልኝ አድርጌ ወደ ናዝሬት ገሰገስሁ።

ከመኪና ወርጄ ወደ ሆስፒታል ስሄድ በመንገድ አንድ የሆስፒታል ሠራተኛ አግኝቶ "አዲስ አባት ሚሊዮን" ይሉኛል እያልኩ አጓዝ ነበር፡፡ ማንም አልገጠመኝም፤ ተስፋ ሳልቆርጥ ግቢው ዉስጥ እንደገባሁ ግራና ቀኝ እያየሁ ጠበኩ ማንም አላለኝም። በቀጥታ ወደ ሆስፒታሉ የነርሶች ቢሮም ስሄድም ምንም አላሉኝ። አሁን አፍ አውጥቼ "እንዴ ስለ ግደይ የምትነግሩኝ የለም እንዴ" ስላቸው "ምንም የምንልህ የለንም ያረፈቺው ዶክተር ዮደር ቤት አይደለም እንዴ?" አለች አንዷ፤ "ምጥ ላይ መሆንዋን ሰምቼ ነው የመጣሁት" ስል ሴላይቱ "እንደዛ ከሆነ ቁጥር አንድ ትሆን ይሆናል" ስትል ቶሎ ወደ እዚያ ሄድሁ፡፡ በሩን ከፍቼ ስገባ እህቷ ንግስቲና አንድ ነርስ አጠገቧ አሉ፤ እርሷ አልጋ ላይ ተጋድማለች፡፡

ትንሽ እንደቆምሁ ግደይ ጩኸቷን ለቀቀቺው፥ ደነገጥሁ፡፡ የምጥ ጣር መሆኑን አላውቅሁም፡፡ ተርበተበትኩ ነርሷ "ምንም አይደል" ብላ አረጋጋቺኝ፡፡ ግደይ ቆየት ቆየት እያለች ትጮሃለች፤ ንግስቲ "አንቺ ዝምበይ አታስድቢን" ትላታለች፤ እኔም "በርቺ እንጂ" እላለሁ የማይጠቅም ምክራችን ሲበዛባት "ሄዱልኝ"

ትለናለች።

በየአምስት ደቂቃ የግደይን የምጥ ስቃይ ስንሰማ ቆይተን አማኑኤል ለመዉጣት ስላቅማማ የሚያፋጥነው መድሃኒት እንዲሰጣት ወደ ማዋለጃ ክፍል ተወሰደች፤ ዶክተሩ፣ ነርሷ፣ ድሬሰሮቹ ልብሳቸውን ሰብሰው እርሷን መውሰጃው አልጋ ላይ አስተኙዋት፤ እኔም ጎንዋ እንድቆም ተፈቀደልኝ፡፡ አሁንም ቆየት ቆየት እያለች መጮኋን አላቋረጠችም፡፡ አ! በይ፡ አ! በይ እያሉ ኢተር አሸተቷት፣ ጥቂት ቆየት ብላ መቀባጠር ጀመረች፤ 'የሰሙኒ - - አጥታ ነው' . . ውዘተ ትለለች፡፡ በ9:15 አማኑኤል ተመዞ ወጣ፤ መጋቢት 6 ቀን 1952 አማኑኤል ተወለደ፡፡ እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ አባት ሆንሁ።



አማማ ግደይና አማኑኤል





## ዝግጅትና ጉዞ ወደ አሜሪካ

ከአማኑኤል መወለድ በኋላ ግደይንና ልጄን ይዤ ወደ አሜሪካ የመሄድ ፍላጎቴ ከፍተኛ ሆነ፡፡ ብዙ መፀለይና አማራጮችን መፈለግ ጀመርኩ፡፡ ይዣቸው ብሄድ አሜሪካ የማገኘው ሥጋ ባያስበላንም ለዳቦና ድንች ሊበቃን እንደሚችል አውቃለሁ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር በመሄድ ከሚስቴ ጋር እንደምሄድ ገለጥሁላቸው፡፡ "ትችላለህ፣ ነገር ግን ለጉዞውም ሆነ በአሜሪካ ኑሮህ መንግስት ላንተ ብቻ እንጂ ለሚስትህ ምንም አይነት ድጋፍ አያደርግልህም" አሉኝ፡፡

በአሜሪካ ስኖር ለመኖሪያ የሚሆነኝን የሚሰጠኝ የአሜሪካ መንግስት ሲሆን ከአዲስ አበባ አሜሪካ ደርሶ መልስ መጓጓዣ የሚከፍል ትምህርት ሚኒስቴር ነው፡፡ በዚያን ዘመን በአውሮፕላን ለመሄድ 1,500.00 ብር በመርከብ ለመሄድ 1,000.00 ብር መሆኑን ስለተረዳሁ ሚስቴን በመርከብ ይዤ እንድሄድ ትምህርት ሚኒስቴር የሚከፍለውን 1,500.00 በጥሬ ገንዘብ እንዲሰጠኝ ብጠይቅ አይቻልም አሉኝ። ለሚስቴና ለልጄ 1,000.00 ብር እንደሚያስፈልገኝ ተረዳሁ። ወደ አሜሪካ ብቻዋን እንዴት ትሄዳለች የሚለው አሳሰበኝ፤ መጸለይ ቀጠልኩ።

በዚያን ጊዜ ሚሲዮኖች የሚጓጓዙት በመርከብ ስለሆነ ወደ አሜሪካ የሚሄዱ ሚሲዮናውያን ማፈላለግ ጀመርሁ፡፡ በተመሣሣይ ወቅት ለዳንኤል ለማና ለአርያም ዘካርያስ (አጮኛሞች) የእኛው ሚሲዮን ስኮላርሺ ሰጥቶ ነበር። ግደይ ከእነርሱና ከሌሎች የኤስ. አይ. ኤም. ሚሲዮናውያን ጋር በመርከብ (ከጂቡቲ እስከ ኒውዮርክ) መጓጓዝ እንደምትችል ታወቀ፡፡ ነገሮች መገጣጠም ጀመሩ፤ አሁን የቀረው ለመርከብ ጉዞው 1,000.00 ብር፣ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ ለአይሮፕላን ትኬትና የኪስ ገንዘብ ማግኘት ነው፡፡ ጎጆ የወጣንበትን እቃ፣ ከአሜሪካ ስመለስ ያመጣኋቸውን እቃዎቼና ልብሶቼ ሣይቀሩ ዋጋው 25 ሳንቲም የሆነ ነገር ሁሉ እየሸጥን ማጠራቀም ጀመርን፡፡ ከጂቡቲ እስከ ኒውዮርክ የምትሄደው የእቃ መጫኛ መርከብ መነሻዋ መቼ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ በዚያች መርከብ እንዲጓዙ አስመዘገብሁ፤ ቀኑ ሲቃረብ ለመርከብ ከፈልሁ።

በእኔ ቤት ከእኔ የሚፈለገውን ሁሉንገር አድርጌ ጨርሻለሁ:: ከጂቡቲ የሚነሳው መርከብ ሶስት ቀን ሲቀረው ሲል ከአዲስ አበባ ጂቡቲ ለመጓዝ፣ በአይሮፕላን ቦታ ለመያዝና ቲኬት ለመግዛት ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ቲኬት ቢሮ ሄድሁ:: አይሮፕላን ሙሉ ነው አሉኝ:: ጉድ ፈላ! እረ እንዴት ተደርጎ! መሄድ አለብኝ! ብዬ ማልቀስ ቀረኝ:: ግራ በመጋባት እየተወራጨሁ የአየር መንገዱን ሠራተኛ እንዳች መውጫ ዘዴ እንዲፈልግልኝ ተማጠንሁት:: ቦታ አልያዝከም እንዴ? ስሚ ማንነው አለኝ? ነገርኩት:: ስውዬው ማየት ጀመረ ቦታ አስማስያዜን እያወኩት ሲፈልግ ዝም ብዬ በተስፋ እጠብቃለሁ:: የተፃፉትን ስሞች በመደዳ እንብቦ "እ... እ ... ተይዞአል ከፈል" አለኝ:: የሚናገረውን ማማን እቃተኝ ... ሳላቅማማ ከፍዬ ወጣሁ። ተዓምር ነው::

"መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ እርሱ ያቃናልሃል" የሚለው ተፈጸመ:: አቀድምልሃለሁ የሚለኝ ጌታ ቀድሞልኝ አየሁ። ተሳፍራ ሄደች። ከሄደች በኋላ በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ እግዚአብሔር ያደረገውን ስመስከር፥ ሚስተር ሴንስኒንግ ከሳምንታት በፊት ለእነ ዳንኤል ቦታ ሲይዙ ስግደይም እንደያዙ ነገሩኝ:: አምላኬ የእኔን መዝረክረክ ለለሚያውቅ ቀደም ብሎ በዳንኤል ሴንስኒንግ አማካይነት ለግደይ ቦታ አለያዘላት፤ አምላኬ ቀደመልኝ። እኔ የቀሩትን እቃዎቻችንን ሸጬ የተረፈቺኝን ገንዘብ ለአሸብር ሰጥቼ በተውሰነልኝ ቀን እኔም ወደ አሜሪካ በረርሁ።

## ኑሮ በአሜሪካና ትምህርት

ዋሺንግቶን እንደ ገባሁ ወደ International Cooperation Administration ቢሮ ሄድሁ:: እንደ.ልማዳቸው አስፈላጊው መግለጫና የምማርበት ት/ቤት ከነገሩኝ በኋላ ሚስቴንና ልጄን ለመቀበል ወደ ኒውዮርክ ሄድሁ:: ተቀበልኳቸውና ጊዜ ስለነበረኝ ወደ ላንካስተር ሄደን እማማና አባባ ኪነር ቤት አረፍን።





ስለቀጣዩ ኑሮአችን ማቀድና ማሰብ ጀመርን:: ከዚያም የተመደብኩበት ት/ቤት የሚገኘው ፊላደልፊያ (Philadelphia) ስለሆነ ወደ እዚያው ሄድን:: የተመደብኩት ፔንስልቫኒያ ዩኒቨርስቲ (University of Penslvania) ስለሆነ ወደ እዛ አመራሁ:: ኖርስ ስኳር ሜኖናይት ቤ/ክ (Nores Square Mennonite Church) ግቢ ዉስጥ ባሉት እንዷት አፓርትማ ዉስጥ በነፃ እንድኖር ስለፈቀዱልን እዚያ እየኖርሁ በምድር ዉስጥ ባቡር እየተመላለስሁ ትምህርቴን ጀመርኹ።

ሜኖኒይቶች ከአዲስ አበባ ጀምሮ ያደረጉልን ድጋፍ እጅግ ብዙ ነው:: ካደረጉልን ጥቂቶቹ፣ የአሜሪካ ኢምባሲ ስግደይና ስሕፃኑ አማኑኤል ቪዛ እንዲሰጠን ደብዳቤ በመጻፍ፣ ፊለደልፊያ መኖሪያ ቤት በመስጠት፣ በአሜሪካ ኑሮ ስንጀምር የቤት ዉስጥ ቁሳቁስ በመስጠት ረዱን።

ፊላደልፊያ አራት ወር ከኖርን በኋላ የዩኒቨርሲቲው ትምህርት ፕሮግራም ስኔ ስላልተስማማኝ ወደቀድሞዉ ት/ቤቱ ወደ ዌስተርን ሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ ተዛወርሁ:: ስለዚህ ወደ ካላማዙ ሄደን ኑሮንና ትምህርቱን ተያያዝኩት:: በወር ከማገኛት 210.00 ዶላር 60 ዶላር ለቤት ኪራይ በመክፈል ቤተሰብ ላላቸው ተማሪዎች ከተመደቡት ቤቶች አንድ ተከራየሁ:: በካላማዙ ከተማ ካሉት ጥቂት ሜኖኒይቶች ጋር ወዲያው ተዋወቅን:: ከእነርሱ ጋር ከማምለካችንም በላይ ምክራቸውን ይሰግሱን ነበር:: እነርሱም በዚያ ኑሮ እንድንጀምር ረዱን። እኔ እንድሠራ አይፈቅድልኝም፤ ግደይ ዶክተር ፊዘርበርት ጥሩ የድጋፍ ደብዳቤ ጽፉላት ስለነበር ያን ይዛ ወደ አንድ ሆስፒታል በመሄድ ሥራ ጠይቃ አገኘች። የሥራ ፈቃድ ስለሚያስፈልጋት ሆስፒታሉ አመልክቶ ፈቃድ እንዲሰጣት ተደረገ፡ በየሁለት ሳምንቱ 92.00 ዶላር ማግኘት በመቻልዋ ከበርን:: ወደ ሱቅ ሄደን ልብስና ሌሎችም ነገሮች መግዛት ቻልን። በጥንቃቄ መኖርን መርሃችን አደረግን፤ ለምሳሌ ጸጉሬን ለመስተካከል በየወሩ 3 ዶላር ከመክፈል ጉብያ ሄጄ አንድ ቶንዶስና መቀስ በ4.00 ዶላር ገዝቼ ግደይ እንድትቆርጠኝ አደረግን:: ለመጀመሪያው ጊዜ ስታስተካክለኝ ገጣጥባ ሰቀቀችኝ፤ ደግነቱ ይህን የሚያስተውል አልነበረም፤

ልዩነቱን የምታየው እርሷው ነበረች፤ በኋላ ግን ቻለችበት።

አሜሪካ ያለመኪና ለመኖር አይቻልም ስለዚህ አንዲት መኪና በ150.00 ዶላር ገዛሁ:: መንዳት ተማርሁ:: የመኪና መንጃ ፈቃድ ለማግኘት አንዲት ትንሽ መጽሐፍ ገዛሁና አንብቤ ለፈተና ሄድሁ 97 ከመቶ በማግኘት አለፍሁ:: ፈታኟ "አይንህ እንዴት ነው?" አለቺኝ፤ "ጥሩ ነው" አልኳት በልበ ሙሉነት:: "እስቲ ያን አንብብ" በማለት እዚያው የማየት ችሎታዬን ፈተሸችው:: "መነጽር ያስፈልግሃል" አለቺኝ:: ማለፌን የሚገልጽና ጊዚያዊ የመንጃ ፈቃድ ስትጽፍ ግን በስህተት መነጽር አያስፈልገውም ብላ ጽፋ ለተግባር ፈተና ቀጠሮ ይዛ ለቀቀቺኝ። ተግባሩን የፈተነኝ ሽማግሌ "እንግዲህ በተለይ በበረዶ ላይ ስትነዳ ተጠንቀቅ" ብሎ ማለፌን ፈርሞ ሰጠኝ። የመንጃ ፈቃድህ በፖስታ ይላከልሃል ተብዬ ጊዚያዊ መንጃ ፈቃድ ተላከልኝ።



የመጀመሪያ የቤተሰብ ፎቶ 1954 ዓ ም ካላማዙ ሚቺጋን

በመኪና ግደይን ወደ ሆስፒታል ማመላለስ ጀመርሁ። አንድ ቀን አድርሼያት ስመለስ አይን መርምሮ መነጽር የሚሸጥበት ሱቅ መኖሩን ሰምቼ እየነዳሁ





መፈለግ ጀመርኩ:: ሱቁ አጠገብ ስደርስ፣ መኪናዬን ለማቆም ቦታ ስፈልግ በሃይል ጓ! ብላ መኪናዋ ቆመች:: በድንጋጤ ስመለከት ከኤሌትሪክ ምሰሶ ጋር ተጋጭቼአለሁ:: ጩኸቱ ለእኔ ከፍተኛ ስለነበር አገር ሁሉ የሰማኝ ነበር የመሰለኝ:: ዞር ዞር ብዬ ሳይ ማንም ወደ እኔ የሚመለከት የለም:: እንደምንም ተንፏቅቄ ወደፊት በመሄድ ቀጣዩ ነዳጅ ማደያ ደረስሁ:: ወርጄ ሳይ መኪናዋ የፊቷ ፈረፋንጎ ተደፍጥጦ የፊት ጎማው ተቀርድዷል:: ባለመንጠቆ መኪና አምጥተው ከጎማዬ ጋር የተጣበቀውን በመፈልቀቅ አላቀቁልኝና ጎማህን ለውጥ ብለው 8.00 ዶላር አስከፈሉኝ:: ወጪው ቢያንገበግበኝም ከፈልኩ::

ግደይ የምትሠራው ከሰዓት በኋላ ከ9 ሳዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት ነበር። አማኑኤልን መጠበቅ እንድንችል የኔን የትምህርት ፕሮግራሞች ጠዋት ጠዋት



ከዌስተር ሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ የተመረቅሁ ለት

እንዲሆኑ አደረግሁ። እልፎ አልፎ ከሰዓት በኋላም የሚሰጥ ትምህርት ነበረብኝ፤ በእነኚህ ቀናቶች አብሮኝ የሚማር ሳሙኤል አዋሎም አማኑኤልን ይጠብቅልን ነበር:: (ከሳሙኤል ጋር ወደጅነት ቀጥሎ ባህርዳር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲቱት የሥራ ባልደረባዬ ነበር፤ ሲያገባ ሚዜው ነበርሁ።)

እንዲህ ተረዳድተን ትምህርቴን በሰኔ ወር 1954 ዓ.ም. ጨርሰሁና ወደ አገሬ በመርከብ ተመለስሁ።

## መንፈሳዊ ሕይወት በአሜሪካ

መጀመሪያ ተማሪ በነበርኩበት በካላማዙ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን አልነበረም። አሁን ግን አብረን የምናመልክና የምንጠያየቅ ቤተሰቦችን አገኘን፤ አንድ ሰው ለአጭርም ጊዜ ይሁን ለረጅም ጊዜ በሚኖርበት አካባቢ የአምልኮ ቦታ ያስፈልገዋል፡፡ አብርሃም፣ ይስሃቅና ያዕቆብ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ባረፉበት ቦታ ሁሉ መጀመሪያ የሚሰሩት መሰዊያ ነበር፡፡ በሄድንበት ሁሉ የምናመልክበት፣ የምንገለገልበትና የምናገለግልበት ቤተክርስቲያን ያስፈልገናል። የካላማዙዋ ሁብረት እራሳችንን እንደ ጊዜያዊ አባል አድርገን የምንቆጥርባት ነበረች። በዚያች የሰንበት ክፍል አስተማሪና ሽማግሌም ሆኜ በማገልገሌ በክርስትና ህይወቴ እንዳድግ ረድቶኛል፡፡

ቢሾፓችን ከዚያ 30 ማይልስ ራቅ ብላ በምትገኝ ከተማ የሚያገለግል የቀድሞው ፓስተራችን ኤትሮል ላይንቦክ ይባላል፡፡ እርሱና ቤተሰቡ እኛን በመንፈስም በሥጋም ይረዱን ነበር፡፡ ለልዩ ልዩ ስልጠናዎች ለቀናት ስሄድ ግደይና አማኑኤልን እነርሱ ጋር ይቆዩ ነበር፡፡ ለአማኑኤል "ማኒ" የሚል ቅጽል ስም የሰጠችው ባለቤቱ ነበረች፡፡ (ከእነርሱ ጋር ግንኙነታችን ቅርብ ስለነበር እስከ ናይሮቢ ድረስ በመምጣት ጎብኝተውናል) 40 ማይልስ ራቅ ብላ የምትገኘው የባትልክሪክ ከተማም ሜኖኒይት ቤተ ክርስቲያን ታቀርበን ነበር፡፡ የመርል ብራዘርስ ልጅ ሜይ ስታገባ እኔና ግደይ ሰርጉ ላይ በአማርኛ የአምላክ ፍቅር የሚለውን መዝሙር ዘምረናል። እንዳለፈው ጊዜ ከኢንተር ቫርሲቲ ጋር ግንኙነት ማድረግ አልቻልኩም፡፡ እነርሱ የሚሰበሰቡት ማታ ማታ ስለ ነበር ግደይ ሥራ ስለምትሆን አማኑኤልን መጠበቅ ነበርብኝ። ከእነርሱ ጥቂቶቹ እየመጡ ይጠይቁኝ ነበር።

በዚያን ዘመን በክርስትና ሕይወቴ በጣም የጠቀመኝ የራዲዮ መፍሃፍ ቅዱስ ትምህርት (RADIO BIBLE CLASS) የሚባል ነበር። ሰባኪው በወጣትነቱ ጊዜ ከሃዲ የነበረ ዶክተር ኤም አር ዲሃን (Dr. M. R. DeHaan) የተባለ ሰው ነበር፡፡ ክርስቲያን በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል እያነበበ የመጸለይ ልምድ





ያስፈልገዋል የሚል በየወሩ የእለት እንጀራ (OUR DAILY BREAD) የምትል ጽሁፍ እያሳተመ ይልክ ነበር፡፡ ይህ አገልግሎት አሁንም አለ፡፡ ትምህርቱ በጣም ይጥመኝና ይጠቅመኝ ነበር። ሌላው የማያመልጠኝ ፕሮግራም የቢሊ ግርሃም (BILLY GRAHAM The Hour Of Decision) የተባለው ፕሮግራም ነበር። እነኚህን ሁለት ፕሮግራሞች በቴፕ ሪኮርደር እየቀዳሁ ደግሜም እዳምጣቸው ነበር። (በኋላ ላይ የቀረጽኳቸውን መልእክቶች ወደ ኢትዮጵያ ይዤአቸው መጥቼ መቀሌና ባህር ዳር በነበርኩበት ጊዜ ተማሪዎች እንዲሰሟቸው አደርግ ነበር፡፡)

## ምዕራፍ 7

# ወደ አገሬ መልስ

### ወደ አገሬ መልስ

ከዌስተርን ሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ በሰኔ ወር 1954 ዓ.ም (1962) በኤሌትሮኒክ ቴክኖሎጂ ተመረቅሁ፡፡ ወደ አገሬ ስመለስ እኔ በአይሮፕላን መመለስ እችላለሁ ነገር ግን ለግደይና ለአማኑኤል የአይሮፕላን ቲኬት ለመክፈል ስለሚከብድብኝ ከእነርሱ ጋር በመርከብ ለመመለስ ወሰንሁ፡፡ በመርከብ መሄድ ስለምፈልግ ከቤተሰቤ ጋር ለአይሮፕላን የሚከፈለውን ገንዘብ ሰጡኝ ብላቸው አሁንም አምቢ አሉኝ፡፡ በአንዲት የግሪክ የጭነት መርከብ ከኒውዮርክ እስከ ጂቡቲ ተጓዝን፡፡ ጉዞው አንድ ወር የፈጀ ነበር፡፡ ከኒውዮርክ ከተነሳን በኋላ መጀመሪያ የቆምነው ክሬት የምትባል የግሪክ ደሴት ነበር፡፡ ከክሬት እስከ ጂቡቲ ሌላ 15 ቀን ወሰደብን፡፡ በየወደቦቹ ስንቆም እንጐበኝ ነበር፡፡ አሌግዛንደሪያ ስንቆም ካይሮ ድረስ ሄደን ስመጎብኘት ችለናል።



በ1954 ከአሜሪካ ወደ ሃገር ቤት ስንመለስ መርከባችን አሌግዛንደሪያ ቆም ብላ ስለነበር ወደ ካይሮ መጥተን ፒራሚድን ስንጎበኝ





ጉብኝታችንን በመቀጠል እየሩ በጣም የሚሞቅ የሳውዲ አረቢያ ወደብ ደረስን። እንዴት እንደተቀነባበረልን ባላስታውስም የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት በመርሲዲሳቸው ወደ ቤታቸው ወሰዱን፡፡ ሠራተኞቻው ከአገር ቤት የመጣላትን ድርቆሽ በአንፋሎት አለስልሳ ከውጥ ጋር አቀረበችልን፡፡ ግደይ ለሁለት አመታት ያህል ያላገኙቸው እንጀራ ከወጥ ጋር ሲቀርብላት እንጀራ በማግኘቷ በደስታ ልቅሶ ጭምር ነበር የተመገበችው፡፡ ካላመዘ ስንኖር እንጀራ ለመጋገር ብዙ ጊዜ ሞክራ ሳይሳካላት ቀርቷል፤ (ዱሮ ውጭ አገር የሄድን በጣም የሚናፈቀን እንጀራ በወጥ ነበር፤ ወደ አገራችን የሚያሮጠን አንዱ ነገር ይሄ ይሆን?)፡፡

ጂቡቲ እንደ ገባን ሁለት ቀን አድረን በባቡር ወደ ድሬዳዋ ተጓዝን፡፡ ወዲያው መጓጓዣ ባቡር ማግኘት አልቻልንም፡፡ ሁለት ቀን አድረን በማታ ባቡር ተሳፍረን በሚቀጥለው ቀን ድሬዳዋ ገባን፡፡ ወደ አዲስ አበባ የሚወስድ ባቡር ከሁለት ቀን በኋላ ስለነበር ያለው እቃችንን ድሬዳዋ ሜኖናይት ሚስዮን ግቢ አስቀምጠን ወደ ደደር ሄድን፡፡ አባዬ የምትኖረው ሆስፒታሉ አጠገብ ስለ ነበር ማደሪያችን ከነርሶች ቤት አድርገን እርሷ አስተናገደችን፡፡ ከነርሶቹ አንዷ ጆኒ ዚመርመን (አሁን ጆኒ ዉሂበ) ነበረች፡፡ በዚያን ጊዜ አማኑኤል አማርኛ ስለማይናገር "አማርኛ በመናገር የምበልጠው ኢትዮጵያዊ አገኘሁ" በማለት በደስታ ፎከረች። ደደር አንድ ቀን አድረን ወደ ድሬዳዋ ተመልሰን በባቡር አዲስ አበባ ገባን።

### ሥራና አገልግሎት በመቀሌ

ከአሜሪካ ስመለስ የባህርዳር የቴክኒክ ት/ቤት ግንባታው ስላላለቀ ለአንድ አመት ወደ መቀሌ ተላከሁ፡፡ በዚያ ያለው የአጼ ዮሃንስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እንዲሆን ታስቦ ስለነበር የቴክኒኩን ክፍል እንዳደራጅ ወደ መቀሌ ተላክሁ፡፡ በአዲስ አበባ ያሉ ወገኖች ወደ መቀሌ እንደምሄድ ስነግራቸው "ለምን ወደ እዚያ ትሄዳለህ? እዚሁ አዲስ አበባ ሥራ እንዲሰጡህ ለምን አትጠይቅም?" መቀሌ ያንተ ብጤዎች (ወንጌላውያን ማለታቸው ነው) የሉም" አሉኝ፡፡ እኔም ስመልስ "ታዲያ ምን አለ? ትግሬይ እኮ በኢትዮጵያ

ክርስትና የተጀመረበት ቦታ ነው፣ ፍሬምናጦስና ወንድሙ በአክሱም ቤተ መንግሥት የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን ነበሩ አኔስ ወንጌላዊ ሆኜ ብሄድ ምናለበት" በማለት እመልስላቸው ነበር፡፡ የወንጌል ሥራ ለመጀመር በመቀሌ ከተማ መጻሕፍት መደብር በማቋቋም ስመስራት በማሰብ ከሜኖ መጻሕፍት ቤት ጋር እንዴት ሊረዱኝ እንደሚችሉ ተነጋግሬ ቤተሰቤን ይዤ በአውቶቡስ ወደ መቀሌ ሄድሁ፡፡ በዚያን ዘመን ለኛ የሚስማማ የሚከራይ ቤት ማግኘት በጣም ከባድ ነበር፡፡ የቤቱ ባለቤት አዚያው የሚኖሩበት በአንድ ግቢ ዉስጥ ቤት አገኘንና ተከራይተን መኖር ጀመርን፡፡

## የመቀሌ ቻፕል መከፈት

ኑሮ በመቀሌ መልካም ነበር፡፡ አንድ ነገር ግን ጎድሎናል ጸሎት ቤት አልነበረንም። በከተማው የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን የለም፡፡ ስለዚህ በቤታችን አምልኮ መጀመር አለብን በማለት አሰብሁ፡፡ ቤት ሆኜ ግቢያችን ዉስጥ አንዲት ሴት በትግርኛ መዝሙር ስትዘምር ሰማኋት፡- የምትዘምረውም

ምንም ቢሆን ተስፋ አትቁረጥ አምላአከ ይረዳሃል፣
በፍቅሩ ከንፉ ሥር ብትኖር አምላክ ይረዳሃል፤
አምላክ ይረዳሃል ቀኑን ሁሉ በመንገድህ፣
እርሱ ይረዳሃል አምላክ ይረዳሃል። የሚለውን መዝሙር ነበር።

ይህን ለመዘመር ከወንጌላውያን ጋር ንክኪ እንዳላት ጠረጠርኩ፡፡

ግደይ ቤት ስለምትውል ልጇቱን ለማነጋገር ዕድል ነበራትና ከአድዋ ሚሲዮን ት/ቤት የመጣች ልጅ መሆኗን፣ የግቢው ባለቤት አጎትዋ መሆናቸውን፣ ለሚ ፀሐይነሽ ኃይለ ሥላሴ እንደሚባል ነገረችኝ፡፡ የመጀመሪያው እሁድ አምልኳችን ከእኔ፣ ግደይና አማኑኤል ጋር ሆና በቤታችን እንድታመልክ ጋበዝናት፡፡ ያን እሁድ አራት ሆነን አብረን አመለክን፡፡ ለሚቀጥለው እሁድ ከአድዋ ሚሲዮን ት/ቤት የመጡ ጓደኞቿ ከእኛ ጋር ያመልኩ ዘንድ እንድትጋብዛቸው ነገርናት።





በሁለተኛው እሁድ ዘጠኝ ሆነን አመለክን፡፡ በሦስተኛው እሁድ 15 ሆንን፤ ቤታችን ሞላ፡፡

ስሚቀጥለው እሁድ ቤት ፈልገን ተከራይቱ አዚያ እናመልካለን ብዬአቸው፡ ቤት ካገኘን ፀሐይነሽ እንደምትነግራቸው ካልተገኘ ወደ እዚህ እንዲመለሱ ተነጋግረን ተለያየን። ለጸሎት ቤት ሊሆን የሚችል ቤት አገኘሁ፤ ገበያ ሄጄ ጣውላ ብጤዎች (ጠርቦች) ገዛሁና አንድ አናጢ መቀመጫዎች እንዲሠራልኝ ሰጠሁት፡፡ መቀመጫዎችና አትሮኖስም ሠራልኝ፡፡ ቻፕላችን (ጸሎት ቤታችን) የት እንደሆነ ለፀሐይነሽ ስለ ነገርኳት ከእሷ የሰሙ ተማሪዎች ሁሉ መጥተው በአዲሱ የኪራይ ቤት ማምለክ ጀመርን፡፡ ለሌሎችም ነግራ ስለነበር ቁጥራችን በርክት አለ፡፡ በዚያ ሲጀመርኩት አገልግሎት እንደ ረዳት ሆኖ የረዳኝ ምስግና የሚባል አገኘሁ። አዲስ አበባ የአንድ አመት የመምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት በሚከታተልበት ወቅት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ይሄድ ነበር፡፡ በወቅቱ የመቀሌ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ነበር።

ሌላው የአገልግሎት መንገድ አዲስ አበባ ሆኜ አስቤበት የነበረውን የመጽሐፍ መደብር መከፈት ነበር፡፡ "ብርሃን መጽሐፍ መደብር" በማለት የሰየምኳት መደብር ተከፈተች፡፡ የምሸጣቸውን መጻሕፍት ሜኖ መጽሐፍ ቤት በአውቶቡስ ይልከልኛል። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ የት/ቤት መጻሐፍት ቢሆኑም መጽሐፍ ቅዱስና በዚያን ጊዜ በአማርኛ የታተሙ መንፈሳዊ መጻሕፍትንም ጨምረው ይልኩልኝ ነበር፡፡ ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ በጣም እነጋጋሪ የነበረው "ተግሣፅና ምክር" ነበር፡፡ ሌሎቹ በኤስ. አይ. ኤም. እየታተሙ የሚወጡ መጻሕፍት ነበሩ። ብርሃን መጽሐፍ መደብር በከተማው ያለው ብቸኛው የመጽሐፍ መደብር ስለነበር እንደ ወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐ ብሔር ሕግ ያሉ ተፈላጊ መጽሐፎችም ይሸጡ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች ወደ መደብሩ መምጣት ጀመሩ፡፡

የቻፕሉ አግልግሎታችን ብዙ ተቃውሞ ገጠመው፡፡ በድንጋይ መደብደባችን እንኳ ቤትዋን ያከራዩንን ሰው "እንዴት ለጸረ ማርያም ታከራያለህ" የሚል ንቀፋ

ገጠማቸው፡፡ እርሳቸውም "የማርያም ጠላት የሚያስብላቸው ምንም ነገር እላየሁም፤ ከዚህም በላይ ቤቴ ለብዙ ጊዜ ተዝግቶ ቆይቷል፤ አሁን ተከራይ ስላገኘሁ አከራይቼዋለሁ" በማለት መለሱ።

ትልቁ ተቃውሞ ከቤተ ክነነት ነበር፡፡ የተቃውሞ ትኩረታቸው በመጽሐፍ ቤቷ ላይ አደረጉ፡፡ "ተግሣፅና ምክር" መጽሐፍን ሰበብ እድርገው ሊይዙኝ ፈለጉ፡፡ የመጽሐፍ ደራሲ ተከሰው ለብዙ ጊዜ የታሰሩ ነበሩ፡፡ ጉዳያቸው ዙፋን ችሎት ደርሶ ጃንሆይ መጽሐፍ ለለጻፈ እንዴት ይታሰራል፤ ተሳስቶ ከሆነ ስህተቱን ለማረም እናንተም ጻፉ ብለው ስለፈረዱላቸው ለጊዜው በዚያው ተገቶ ነበር፡፡

ሊያስከስስ የሚችል ግን "የገላትያ ትርጓሜ" የሚባል መጽሐፍ አገኙ፡፡ ይህን መጽሐፍ ሲመረምሩ ማርያም ከኢየሱስ ሌላ ወልዳለች ይላል የሚል አገኙ፤ በገላትያ 1:19 "ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በስተቀር . ." ይላል፡፡ ይህን ጥቅስ ለማብራራት "ማርያም ከኢየሱስ ሌላ ወልዳለችን?" በማለት ይጀምራል፤ ማርያም ኢየሱስን ከወለደችም በኋላ ድንግል ሆና ስለቀጠለች ሌላ እልወለደችም የሚሉ አሉ፤ ወልዳለችም የሚሉም አሉ፤ ደራሲው ወልዳለች የሚሉት የሚያቀርቡትን ምክንያቶችም አስቀምጠዋል።

"እመቤታችን ድንግል ማርያም ከኢየሱስ ክርስቶስ በተጨማሪ ሌላ ልጅ ወልዳለች" ብሏል በሚል ወንጀል ተከሰሼ ፍርድ ቤት እንድቀርብ ከጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት ለከተማው ፖሊስ አዛዥ ደብዳቤ ተጻፈ፡፡ ደብዳቤው የወንጀሉን ፍሬ ነገር በማተት ሁለት ባለ ሥልጣናት በሚገኙበት ቃሌን ተቀብለው ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ የሚያዝ ነበር። ወደ ከተማው ፖሊስ ቢሮ ተጠራሁ። ቢሮአቸው ስደርስ ከሁለቱ ባለስልጣናት ጋር በአክብሮት ተቀብለው ወደ መጽሐፍ መደብሬ እንድንሄድ ጠይቁኝ፡፡ አራታችንም አብረን ሄድን፡፡ ሱቁ ውስጥ እንደገባን ደብዳቤውን አሳዩኝ፤ በመጻሕፍት ቤቱ ያሉትን "የገላትያ ትርጓሜ" መጽሐፎች ይዘን ወደ ቢሮአቸው ተመለስን። የከተማው ፖሊስ አዛዥ አንድ ኮለኔል ነበሩ፤ በሚገባ እንተዋወቃለን፡፡ ለኔ ካላቸው ከበሬታ የተነሳ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመላክ ፈንታ እራሳቸው ቃሌን መመዝገብ ጀመሩ።





"ስምዎን ማን ልበል?" በማለት ጀመሩ - ኮለኔሉ፤

"ሚሊዮን በለጠ"

የትውልድ ዘመን? ግንቦት 22 ቀን 1925 ዓ. ም.

የትውልድ ቦታ? በሐረር ጠቅላይ ግዛት ወበራ አውራጃ ደደር ከተማ እጠገብ

ሃይማኖት? ክርስቲያን

ልዩ ልዩ የክርስቲያን ሃይማኖቶች አሉ፤ ተዋህዶ፣ ካቶሊክ ወዘተ የእርስዎ ምንድነው?

ሃይማኖትህ ምንድነው ለሚለው የእኔ መልስ "ክርስቲያን" ነው፡፡ እኔ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምከተል ስለሆንሁ የእኔ ሃይማኖት ስም "ክርስቲያን" ነው። እንደምታውቁት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም የተጻፈው ይሄው ነው፡፡ "ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ" ነው የሚለው እልኩ።

ባለሥልጣናቱ በመልሴ ተቸግረው ተያዩ፡፡ በጥሞና ንግግሬን ቀጠልኩ፡-

"ኮለኔል፣ ቃሌን እየወሰዱ ነው፤ በመጨረሻም እንደ ሚያስፈርሙኝ ይገባኛል፤ እባክዎ ቃሌን በትክክል ይመዝግቡና ልፈርም" እልኳቸው።

አሁንም ሲቸገሩ አየሁ፤ ቀጥዬም "ሰዎች ፕሮቴስታንት ይሉኛል" አልኳቸው፡፡ "ታዲያ ፕሮቴስታንት ብዬ ልጻፍን?" በማለት ጠየቁኝ፡፡

"እኔ ፕሮቴስታንት መባልን እልወድም፤ እንደምታውቁት ፕሮቴስታንት ማለት ተቃዋሚ እንደ ማለት ነው፡፡ እኔ ማንንም እልተቃወምኩም፣ እልቃወምም፤ እርቶዶክስ ትርጉሙ ትክክለኛ፣ ልክ ማለት ስለ ሆነ እራሴን ኦርቶዶክስ ብል እመርጣለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ከልቤ መከተል ስጀምር ጥሩ እርቶዶክስ የሚያደርገውን ሁሉ እደረግኹ ብዬ እስቤ ነበር፡፡ ነገሩ ረጂም ነው፤ የእኛን ነገር ለማሳጠር እንዲህ ተብሎ እንዲጻፍልኝ እለምናለሁ አልኩ። ሃይማኖትህ? ለሚለው ጥያቄ ክርስቲያን ተብሎ ተጽፎ በቅንፍ (ሰዎች ግን ፕሮቴስታንት ይሉኛል) ይባልልኝ አልኳቸው።

በዚህ ተስማማን፡፡ በራሴ ዋስትና ፍርድ ቤት ስጠራ እንድቀርብ አሳስበው አሰናበቱኝ። መጽሐፎቹ እዛው ቀሩ፤ ተወረሱ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ተጠራሁ፡፡ ሁለት የሥራ ጓድኞቼን ይገናኜ ሄድሁ፤ አንዱ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ወላጆቹ እዚያው መቀሌ የሚኖሩ ሉልሰገድ አለማየሁ የሚባል ነበር፡፡ ሌላው የትምህርት ቤቱ ግምጃ ቤት ኃላፊ ነበር፡፡ እንደ ደረስሁ ሁለት ፋይሎች ታይተው ለሌላ ቀን ተቀጠሩ፡፡ ተረኛው 'ወንጀለኛ' እኔ ሆንኩ፤ ስሜ ሲጠራ ብድግ አልኩ፡፡ በአከራካሪው መጽሐፉ ዉስጥ ስለ ማርያም ሌላ ልጅ መውለድ የተጻፈው ተነበ ወንጀለኛ ለመሆኔ እምነት ወይስ ክህደት ተባልሁ፡፡

"እምነት? ክህደት?" ሲጠየቅ ምን እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ አላወቅም ነበር። መጽሐፉን እኔ እንዳልጻፍኩትና መጽሐፉ የታተመው አዲስ አበባ መሆኑን፤ ሲታተም ሳንሱር ሳይደረግ እንዳልቀረ በመግለጽ ምንም ወንጀል እንደሌለብኝ ለመግልጽ ሞከርኩ፡፡ ብዙ የቃላት መለዋወጦች ነበር። የመንግሥት ሠራተኛ እንደ መሆኔ ሌላ ሥራ መሥራት  እንደማይፈቀድ ስለማውቅ መጽሐፍ ቤቱ የተመዘገበው በግደይ ስም ነበር፡፡  ይህንንም ለመጠቆም ያህል "መጽሐፉን ያስመጣነው አዲስ አበባ ከሚገኘው የሜና ናይት መጽሐፍ መደብር ነው" ስል፣ እንዴት "ያስመጣነው ትላለህ?" በማለት ተቆጡ፡፡ "በብዙኃን የሚናገሩ ጃንሆይ ብቻ ናቸው" ማለታቸው ነበር።

እንደገና ሌላ ማብራሪያ መስጠት ነበረብኝ፤ "ያስመጣነው ስል እኔና ባለቤቴ ማለቴ ነው፤ መጽሐፍ ቤቱ የባለቤቴ የግደይ ነው፡፡ በመጻሐፍት መደብሩ ምን ዓይነት መጻሕፍት መሸጥ እንዳለባቸው በእየዕለቱ ማታ ማታ እንናገራለን፣ በዚያው መሠረት መጽሐፎቹን ከአዲስ አበባ እናስመጣለን"፤ ስላቸው ይህማ ከሆን ተጠያቂዋ ወሮ ግደይ ናቸው፤ እርሳቸው መቅረብ አለባቸው፡፡  ቀጠሮ ይሰጥ እስከዚያ አቶ ሚሊዮን 1000 ብር ያሲዙ፣ ወይም ዋስ ይጥሩ አለያም ማረፊያ ቤት ይቆዩ ተባለ፡፡





ለምናልባቱ ብዬ አብረውኝ የመጡት የሥራ ጓደኞቼን በተራ በተራ ዋስ ስጠራ እንቀበላቸዉም አሉ። በዚህ ጊዜ አለምሰገድ ተቆጥቶ ታዲያ ምን አይነት ሰው ነው የምትፈልጉት? አለ። ዳኛው እንደ መቆጣት ሲሉ ከፍርድ ቤቱ ዉስጥ አንድ ሰው፡ በከተማው ውስጥ ንብረት ያለው መሆን እንዳለበት ገለጹልን፡፡ የኤርትራ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አባል ናቸው የሚባሉ አቶ አዶይ የሚባሉ ባለ ሆቴል መጥተው እንዲዋሱኝ ሊጠይቋቸው ጓደኞቼ ወጡ፡፡ እስከዚያ ከእስረኞች ጋር እንድቆይ ተደረገ።

የተፈለጉት ሰውዬ ታጡ፡፡ መጽሐፍ መደብሩን ያከራዩኝ አቶ ተፈራ የተባሉ ባለ ሆቴል ነበሩ፡፡ እኚህ ሰውዬ "ብርሃን መጻሕፍት መደብር" ብዬ በመከፈቴ ለልጆቻቸው የንባብና ልዩ ልዩ መጻሕፍት ማገኘት በመቻላቸው የተደሰቱ "እኛ አእምሮ የሚያደነዝዝ አልኮል ቤት ከፍተናል፡ አንተ ግን ለልጆቻችን ብርሃን ቤት ከፈትህ" በማለት በጣም ያመስግኑኝ ነበር። "ለመቀሌ ብርሃን አወጣህላት" እያሉም ያሞግሱኝ ነበር፡፡

ጓደኞቼ ወደ እርሳቸው ሄደው ጉዳዩን ሲነግሯቸው፣ ደጋግመዉ፡- "እይ! አይደረግም! አይባልም!" እያሉ ወደ ፍርድ ቤት መጡ፡፡  በቀጥታ ወደ እኔ ቀርበው መነጋገር እንደ ጀመርን፣ ዳኛው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "አቶ ተፈራ ተከሳሹ የመንግሥት ሠራተኛ ናቸው፤ መንግሥት ክሱ በፍርድ ሳይደመደም ሊያዛውራቸው ይችላል፤ ስለዚህም በተፈለጉበት ቀን ሊያቀርቡ ይችላሉ?" አሏቸው፡፡ አቶ ተፈራ ምንም ሳያመነቱ ዋስ ሆኑኝ፤ ተለቀቅኩ።

ቀነ ቀጠሮዬ እስኪደርስ መጽሐፏ ስትታተም የሳንሱር ፈቃድ የተደረግችበትን ደብዳቤ ኮፒ እንዲላክልኝ ወደ አዲስ አበባ ደወልሁ። ኤስ.አይ.ኤም ጉዳዩን ለዋናው አቃቤ ሕግ ሲያመለክት ዋናው አቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ፋይሉ ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ አዘዘ፡፡  በቀነ ቀጠሮው ግደይ ጠበቃ ቀጥራ ከጠበቃችን ጋር ፍርድ ቤት ቀረብን፡፡ ከአዲስ አበባ የተላከውን ደብዳቤ ጠበቃችን ለዳኛው አቀረቡ፤ ፋይሉን ተረክበው ወደ አዲስ አበባ ስለ ተላከ ጉዳዩ በእንጥልጥል ቀረ። እስካሁን ያ ፋይል አልተዘጋም።

የእሁድ ጠዋት የአምልኮ ፕሮግራማችን ቀጠለ፡፡ ሁል ጊዜ መልዕክት አቅራቢው እኔው ነበርሁ፡፡ አዲስ ለሚመጡትም ትምህርት እንዲሆን ልዩ ልዩ ዋና ርዕሶች እየመረጥሁ እሰብክ ነበር፡፡ ስለ ንስሃ፤ ስለ ዳግም መወለድ፤ ስለ ጽድቅ ፤ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ ስለ መንግስተ ሰማይ፤ ስለ ገሃነም እሳት፤ ስለ አሸናፊ የክርስትና ኑሮ፤ ፈተና . . ወዘተ አስተምር ነበር።

የመቀሌው አገልግሎቴ ብዙ ተቃውሞዎች ቢኖሩትም የብዙ ወጣቶችን አይን የከፈተ ነበር፡፡ በዚያ አገልግሎት ተጠቅመናል ካሉኝ መካከል ፀሐይነሽ ኃይለ



የመቀሌ ቻፐል ፊትለፊት

ሥላሴና የኢንጂነር ተካ ገብሩ ባለቤት ሣራ ይገኙበታል፡፡ ሌላው ደግሞ ተከስማርያም ገዛኸኝ ነበር፡፡ ተከስማርያም ከተማሪዎቹ መካከል ዋና ረዳቴ ነበር፡፡ መቀሌን ትቼ ስወጣ መጽሐፍት ቤትዋን ለእርሱ ነበር ያስረከብኩት፡፡ ተከለማርያም አእምሮው በጣም ክፍት የሆነ ሰው ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ "ኢየሱስ ብቻ" ከሚሉት ጋር ገጥሞ በኢትዮጵያ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አጀማመር ዋናው ሰው ሆነ፡፡





የሐዋርያት ቤተክርስቲያን "ሰው መጠመቅ ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ" በማለት የምታስተምር ነች። ከዘመናት በኋላ ተክለማርያምን አግኝቼው እንዴት እንደዚህ ብላችሁ ታስተምራላችሁ? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው" ብሎ አዟል፤ ለምን በኢየሱስ ስም ብቻ ትላላችሁ በማለት ሞግቼው ነበር። የተባባልነውን ማተቱ ስለማይጠቅም በመቀሌ አገልግሎቴ ብዙ እንደጠቀመኝ አስታውሶ ማለፉ ብቻ ይሻላል።

በ1955 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 15 ወጣቶች በመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ ልዩ ሥልጠና ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ በዚያ ሥልጠና ላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተካ ገብሩ ተሳትፎ ነበር፡፡ ተካ ከአመት በኋላ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አገልግሎት በአጼ ዮሐንስ ሁለተኛ ደረጃ በመምህርነት ተመድቦ ወደ እዛ ሄዶ ነበር፤ በዚያች ቻፕል አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ (ከሚስቱ ከሣራ ጋር በዚያ አገልግሎት እንደተገናኙ ራሷ ሣራ ነግራኛለች።)

የዚያ አገልግሎቴ ፍሬ ናቸው ባልልም በሩቅ ሆነው ከሚመለከቱኝ አንዱ አቶ በድሩ ሁሴን ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ "አይጥ በሊታዎች" እንባል እንደነበር በድሩ ነግሮኛል፡፡ በድሩ ወደ ስብሰባችን ባይመጣም ግን ትምህርት ቤት ዉስጥ ብዙ ጥያቄ ይጠይቀኝ የነበረ ተወልደ ዮሐንስ የሚባል ነበር፡፡ ተወልደ አንዱ ጥያቄው "እግዚአብሔርን ማን ፈጠረው?" የሚል እንደነበር ግን ኋላ ራሱ ባይነግረኝ ባላስታወስኩ ነበር፡፡ በዚህ ጥያቄው ምክንያት THE EVIDENSE OF GOD IN AN EXPANDING UNIVERSE የሚል መጽሐፍ እንዳዋስኩት ያም መጽሐፍ የአእምሮውን አይን እንደከፈተለት ነግሮኛል።

በመሠረቱ እኔ ወደ መቀሌ የተላኩት የአጼ ዮሐንስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ አጠቃላይ (Comprehensive) እንዲያድግ የቴክኒኩን ክፍል እንዳቋቁም ቢሆንም፣ በተጨማሪ ግን የዲሬክተሩ የአቶ አሰፋው መላኩ የቅርብ አማካሪም ነበርኩ፡፡ ት/ቤቱ ከአንደኛ እስከ 12ኛ ነው፡፡ ዝቅተኞቹ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዙዎች የሚማሩት በዛፍ ስርና በመጠለያ ዉስጥ ሆነው ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ

በተጨማሪ ት/ቤት ለመግባት የሚያመለክቱ ብዙ ነበሩ። አቶ አስፋው በነገሩ በጣም ተቸገረ፡፡ ከዚህ በፊት የትምህርት ቤት ዲሬክተሩ ሕንዳዊ ነበር፡፡ አስፋው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዲሬክተር ነበር፡፡ አሜሪካ ስለ ትምህርት ተምሯል፡፡ "የፈረቃ ፕሮግራም ብንጀምርስ?" አለኝ፤ አቅዱንም አስረዳኝ፡፡ በዚያን ዘመን የትምህርት አመራር መሠረት በቀን ሰባት ክፍለ ጊዜዎች ነበሩ። እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ 45 ደቂቃ ነው፡፡ በቀን አንድ ክፍለ ጊዜ የጥናት ክፍለ ጊዜ ነበር።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በጠዋት እንዲመጡ፣ አንደኛ ደረጃዎች ደግሞ ከሰአት በኋላ እንዲመጡ በማድረግ፤ ሁሉም በቀን ስድስት ክፍለ ጊዜ ተምረው አንዱን የጥናት ክፍለ ጊዜ በየቤታቸው ያጥኑ አለኝ፡፡ የፈረቃ ትምህርት በኢትዮጵያ የተለመደ ባይሆንም በሌሎች አገሮች ግን የተለመደ መሆኑን ነገረኝ፡፡ በተሰይ በየዘፉ ስር ቁጭ ብለው ለሚማሩት በማሰብ በአቅዱ ተስማማሁ፡፡

ከመምህራን ጋር ተጨማሪ ምክክር ተደርጎ ሁሉም ተስማሙ፡፡ ከዚያ ለተማሪዎች ተነገረ፤ ተማሪዎችም እቤት ሲገቡ ለወላጆቻቸው እንዲነግሩ አደረግን፡፡ በአቅዱ መሰረት ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጠዋት በአንድ ሰአት መግባት ነበረባቸው፤ አንደኛ ደረጆች ደግሞ በሰባት ሰአት መምጣት ነበረባቸው። የፈረቃ ትምህርት በኢትዮጵያ የተጀመረው እንዲህ ባለ ሁኔታ በመቀሌ ነበር። አቅዱ በወላጆች ዘንድ ታላቅ ተቃውሞ አስነሣ፡፡ ልጆቻችንን ግማሽ ቀን ብቻ የሚያስተምር ዲሬክተር መጣብን በማለት ወቀሳው እስከ ትምህርት ሚኒስቴር ደረሰ፡፡ ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ባለሥልጣናት መጡ፤ በውሳኔአችንም ተስማምተው ተመለሱ፡፡

በዚያን ጊዜ ግደይ ሩትን የስድስት ወር ነፍሰ ጡር ነበረች፤ እንደዛም ሆና ባለሥልጣናቱን ቤታችን ጋብዛናቸው ነበር፡፡ እንድትወልድ የምንፈልገው ናዝሬት ኃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል መሆኑንና ወደዛ ለመሄድ ግን መጓጓዣ ችግር እንደሆነ ነግረናቸው ስለነበር ሲመለሱ ግደይ ከእነርሱ ጋር እንድትሄድ በማድረግ መፍትሔ ሰጡን፡፡ ግደይ ከአነርሱ ጋር ወደ አዲስ አበባ ከዚያም ወደ ወዳጆቻችን ወደ ናዝሬት እነ ዶር የድር ቤት አመራች፡፡ ግንቦት 16/1955 ሩትን ወለደች፡፡ ሴት ልጅ በማግኘታችን ደስታ በደስታ ሆንን።





ከወራት በኋላ ወደ ባሕር ዳር ፖሊ ቴክኒክ ኢንስቲቲዩት መዘዋወሬን የሚገልጥ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ የትምህርት አመቱን መቀሌ ጨርሼ ወደ ባሕር ዳር የሚሄዱትን እቃዎቻችን ቀረቃቅቤ ጨረሰኩ፡፡ በመስከርም እቃችን ወደ ባሕር ዳር እንዲላከልን አመቻቸኹ፡፡ ከዚያም መጀመሪያ ወደ አዱስ አበባ ቀጥሎም አዲሲቷን ልጄን ሩትን፣ ትልቁን ልጄን አማኑኤልንና እናታቸውን ለማየት ወደ ናዝሬት ገሰገስኩ፡፡ ክረምቱን ሙሉ እዛው አሳለፍን፡፡ ማረፊያ ይሆነን ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ አንድ የመምህር ቤት ተሰጠን፤ በዚያ የክረምት ወቅት ከመቀሌ ጌታን የተቀበሉ 15 ሰዎች መጥተው ለሁለት ሳምንት ያህል የደቀመዝሙርነት ትምህርት የማስተማር እድል አግኝቼ ነበር።

## ኑሮ፣ ሥራና አገልግሎት በባሕር ዳር

መስከረም (1956) ሲጠባ ቤተሰባችን ማለት ግደይ፣እኔ፣አማኑኤል እና ሩት በሁለት ሞተር አይሮፕላን ወደ ባህር ዳር በረርን፡፡ ወደ መቀሌ በሁለት ቀን የአውቶቡስ ጉዞ ነበር የሄድነው። በአውሮፕላን መሄዳችን ትልቅ ነገር ነበር። ከግማሽ ሰአት በረራ በኋላ ደብር ማርቆስ በሰንበሌጥ የተሸፈነ ሜዳ ላይ አረፍን። አንድ ፈረንጅ ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ሲያርፍ ደንግጦ "በድንገተኛ ነው እንዴ ያረፍነው" (Is this emergency landing?) ብሏል አሉ፡፡ የባሕር ዳሩ አይሮፕላን ማረፊያ ግን ከተማ መሐል ጥሩ ሜዳ ላይ ነበር፡፡ በአንዲት ታክሲ ተሳፍረን ወደ ተዘጋጀልን አዲስ ቤት አመራን፡፡

የትምህርት መማሪያው ሲገነባ ለመምህራንም መኖርያ አንድ ባለ ሶስት ፎቅ ቤት ተሰርቶልናል፡፡ ሶስተኛው ፎቅ ለወንደ ላጤዎች የሚሆን ባለ አንድ መኝታ ቤት ነው፡፡ እኛ ምድር ቤት ባለ ሁለት መኝታ ቤት ተሰጥቶን በደስታ ባሕር ዳር መኖር ጀመርን፡፡

በጣና ሐይቅ ዳር የተመሠረተችው ባሕር ዳር ከአዲስ አበባ 575 ኪሎ ሜትር፣ ከደብረ ማርቆስ 275 ኪሎ ሜትር ከጎንደር ከተማ 175 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ሁለተኛ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እንድምትሆንም ትታሰብ ነበር፡፡ የጢስ አባይንና በጣና ሐይቅ ዉስጥ የሚገኙትን ብዙ ገዳሞች ለመጎብኘት የሚመጡትን ጎብኚዎች የምታስተናግድ ከተማ ናት፡፡ ጢስ አባይ ትኩረቴን የሳበ ክስተት ነበር፡፡ አባይ እንዴት ይጤሳል? ለማየት አጓጉቶኝ ነበር፡፡ እድል አግኝቼ ሳየው አውነትም ይጤሳል። አባይ ከጣና ወጥቶ 20 ኪሎ ሜትር ያህል ከተጓዘ በኋላ ከታላቅ ገደል ላይ ቁልቁል ወርዶ ከስሩ ያሉትን ድንጋዮች ሲመታ ፍንጣቂው ወደ ላይ ሲነጥር ጢስ ይመስላል፡፡ ከበላዩም ቀስተ ደመና ይፈጥራል፤ ይህን ለማየት ጎብኚዎች ካገር ውስጥና ውጪ አገር ወደ ባሕርዳር መጥተው አድረው ጢስ አባይ ወደ ምትባለው ትንሽ ከተማ ይጓዛሉ፡፡ በዚያ የአባይ ወንዝ በከፊል ተገድቦ ኤሌትሪክ እንዲያመነጭ ተደርጓል።

ጢሱን በጉልህ ለማየት መንገዱ ቀላል አይደለም፡፡ እስከ ጢስ አባይ ከተማ በመኪና ጉዞ ከተደረገ በኋላ፤ ከመኪና ይወረድና በእግር ትልቅ ቁልቁለት ይወረዳል፣ የአባይ ወንዝ በሙሉ ተሰብስቦ በሚያልፍበት ጠባብ ቦታ ባለች ከዘመናት በፊት በተሰራች ድልድይ በመሻገር፣ ወገብ የሚፈታተን ዳገት ይወጣና አባይ ፏፏቴ ፊት ለፊት ይደረሳል፡፡ የትዕይንቱ ቦታ እዛ ነው፡፡ ቦታው ላይ ሲቆም በግምት ሁለት መቶ ሜትር ርቆ ድንጋይ ላይ የሚፈጠፈጠው ውኃ ፍንጣቂ እንደ ጭስ ይተናል፤ ቱሪስቶች በአውሮፕላን ወደ ባሕርዳር መጥተው፣ በመኪና ወደ ጢስ አባይ ከተማ ሄደው፣ በእግራቸው ኳትነው እዚህ ቦታ ሲደርሱ በአድናቆት ዋው! ይላሉ።

የአባይ ወንዝ ከጣና ወጥቶ፣ ወደ ደቡብ ይፈሳል፡፡ ጎጃምንና ጎንደርን አካሎ ወደ ምእራብ በመፍሰስ ጎጃምንና ሸዋን ያካልላል፡፡ ወለጋ ሲገባ ፊንጫ ኤሌትሪክ አመንጭቶ፣ ታላቁን ግድብ ሞልቶ፣ ከዚያም ለጎረቤት የሚተርፍ ኤሌትሪክ አመንጭቶ፣ ሱዳን ሲገባ ካርቱም ላይ ከነጭ አባይ ጋር ይገናኛል።





የእኛ አባይ ጥቁር አባይ (BLUE NILE) ያስባለው ከኢትዮጵያ ይዞት የሚሄደው ደለል ነው፡፡ ካርቱም ከተማ ላይ የሁለቱ ወንዞች መልክ በግልጽ ይታያል። (እነዚህ ሁለት ወንዞች ሲገናኙ የማየት እድል አግኝቻለሁ፤ "ወይ ያገሬ አፈር!" በማለትም ተቆጭቻለሁ፡፡) ከዚያም ወደ ሰሜን በመፍሰስ ግብጽ ሲገባ የግብጽን ህዝብ የሚመግበውን የአስዋን ግድብ ይሞላል፡፡ ከግድቡ በኋላ በመስኖ ሰብዙ የእርሻ ልማት ከዋለ በኋላ ቀሪው ውሃ የካይሮን ህዝብ ውሃ አጠጥቶ አሌግዛንደሪያ ከተማ ደርሶ ሕዝቡን ውሃ ካጠጣ በኋላ ሜድተራንያን ባህር ይገባል። ግብጽ የአባይ ወንዝ እንዳይነካባት የምትፍረጨረጨው ለዚህ ነው።

የአባይ ወንዝ ከጣና ወንዝ ይወጣል ይባላል፤ ፈረንጆችም ጣናን የሰማያዊው አባይ ወንዝ መነሻ ያደርጋሉ፡፡ ግን አይደለም፤ አባይ የሚመነጨው ከደብረ ማርቆስ ወደ ሰሜን በኩል ከምትገኝ ተራራ ስር ነው፡፡ ከተራራዋ ስር ሲመነጭ (ግልገል አባይ ይባላል) ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመፍሰስ ጣና ይገባል፡፡ ሌሎችም ወንዞች ከብዙ አቅጣጫ ወደ ጣና ይገባሉ፤ ስለዚህ አባይ ከጣና ሲወጣ ዉኃው በርከት ያለ ይሆናል።

የባሕር ዳር ከተማ የምትገኘው እዚህ ቦታ ላይ ነው፡፡ የቴክኒክ ት/ቤቱም የተሠራው እዚህ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሶቭየት ሕብረትን በጎበኙበት ወቅት ለማስታወሻ መስኮቦች የሠሩልን ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች በ1955 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና (ማለትም ከ8ኛ ወደ 9ነኛ ለማለፍ የሚሰጠውን ብሔራዊ ፈተና) ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ነበሩ፡፡ ግን የተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ከፍተኛ ስለ ነበር ብዙዎቹ ሲከብድባቸው ተገነዘብን፡፡ ስለዚህ ወደፊት የምንቀበላቸውን ተማረዎች አስረኛ ክፍል የጨረሱ እንዲሆኑ አደረግን።

ትምህርት ቤቱ በአዳሪነት 1000 ተማሪዎች ማስተናገድ የሚችልና በአምስት የሙያ መስኮች ማለትም፦ በአግሮ መካኒክ፣ ኤሌትሪክ፣ ኢንዱስትሪያል ኬምስትሪ፣

ቴክስታይልና የእንጨት ቴክኖሎጂ ስማሰልጠን የሚያስችል ነው። መስኮቦች ት/ቤቱን ሠርተው ሲሰጡን በዚያ የሚያስተምሩት መምህራን የምዕራብ አገር ተወላጆች እንዳይሆኑ ገደብ ጥለውብን ነበር፡፡ በመጀመሪያው ሁለት አመቶች አብዛኞቹ አስተማሪዎች አሜሪካ ሠልጥነን የመጣን ኢትዮጵያውያን ብቻ ነበርን። ከሁለት አመት በኋላ ግን በቂ ኢትዮጵያውያን መምሕራን ስላልነበርን ህንዶችና እንግሊዝኛ የሚያውቁ ሩስያኖች ተፈልገው መጥተው እንድዲያስተምሩ ተደረገ።

በመጀመሪያው አመት አብዛኛውን ጊዜአችንን ያጠፋነው በሩስያ የተሠሩትን መሳሪያዎች በማጥናት ነበር፡፡ የሚያስጠኑን አምስት ኤክስፐርቶችና ተርጓሚዎች ነበሩ፡፡ ከባድ ተግዳሮት ነበረብን፡፡ አንዱ በሩስያንኛ የተጻፉትን የመሳሪያዎች መመሪያ (ማኑዋል) ወደ እንግሊዝኛ መተርጎም ነበር።

ከመላው ኢትዮጵያ በስምንተኛ ክፍል ፈተና ጥሩ ውጤት ያገኙ 250 ተማሪዎች ተመልምለው የነበረ ቢሆንም የመጡት 235 ነበሩ፡፡ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ቢሆንም የትምህርቱ ይዘት ግን ከባድ ነበር፡፡ ስመጀመሪያ ጊዜ ከ8ተኛ ክፍል የተቀበልናቸውን በክረምት በማስተማር ፕሮግራሙን እንዲጨረሱ አደረግን፡፡ ይህም በመጀመሪያና በቀጣይ ዙር ተማሪዎች መሃከል የነበረው ልዩነት አስተዳደራዊ ችግር ፈጥሮ ተማሪዎች እስከማደም ደርሰው ነበር፡፡

የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት በባሕር ዳር መከፈት ስከተማዋ መስወጥ በዋናነት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ቀደም ብሎ የተከፈተው የጥጥ ፋብሪካ ለከተማው ዋና የኢኮኖሚ ለውጥ ያመጣ ቢሆንም ታላቅ የማህበራዊም ለውጥ የጀመረው የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት መከፈት ነው፡፡ ከማህበራዊ ለውጦቹ መሐከል አንደኛው የተቋሙ መምህራን አኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ በአቢይ ጾም ጊዜ ሉካንዳዎች ስስሚዘጉ፡ አስተማሪዎቹ አንዲት መሲና አርደው ቅርጫ ተከፋፈሉ፡፡ ይህም በከተማው ተሰማ፡፡ ጉድ ተባለ! ቄሶች ተሰብስበው ወደ አውራጃ አስተዳዳሪ በመሄድ አቤት አሉ፡፡ አስተዳዳሪው የተማሩና ዘመኑን የሚያውቁ ስለነበሩ አስረድተው አሰናበቷቸው፡፡ ሌላው ማህበራዊ ስውጥ እኔ በቤቴ የጀመርኩት እምልኮ ነበር፡፡ ዝርዝሩን ዝቅ ብዬ አገልጻስሁ፡፡





ወደ ባሕር ዳር በመምህርነት ነው የመጣሁት፡፡ በወቅቱ ዲሬክተሩ በከሪ አብዱሳሂ (አሁን ዶክተር) ነበር፡፡ በከሪ ጎበዝ ነው፤ ዲሬክተር የሆነው ከሁላችንም በትምህርት ደረጃ ስስ በስጠ አልነበረም፤ ከሁላችንም በፊት ቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የትምህርት ቤቱ የመጨረሻ ግንባታ ላይ ከመስኮቦቹ ጋር ሠርቶ ስለነበረ ጭምር ነው፡፡ አኩያችን በመሆኑ አብዛኞቹ መምህራን አስቸገሩት "ከኛ እኩል ሆኖ እንዴት የኛ አለቃ ይሆናል" በሚል ስሜት አስጨነቁት፡፡ በበኩሌ ዲሬክተሬ በመሆኑ ምንም ቅሬታ አልነበረኝም ነበር፤ ይህን ስስተረዳ ይመስለኛል ስሥራ ወደ አዲስ አበባ በሚሄድበት አጋጣሚ ሁሉ እኔን ወክሎ ነበር የሚሄደው፡፡

በከሪ ከአስተማሪዎች ጋር መግባባት አልቻለም ተብሎ እርሱን ወደ ሌላ አዛውረው የወይዘሮ ስሂን ት/ቤት ዲሬክተር የነበረውን አቶ ይፍሩ ገበየሁን ከደሴ አመጡልን፡፡ በእውነቱ ከሆነ በዲሬክተርነት ልምድ ማካበቱ እንጂ የትምህርት ደረጃው ከእኛ ጋር እኩል ነበር። ይፍሩ ጎበዝ ዲሬክተር ነበር፡፡ በማስተማሩና በማደረጃጀቱ ከጎኑ አልተለየሁትም ነበር፡፡ በአመቱ መጨረሻ እኔም ምክትል ዲሬክተር ሆኜ ተሾምኩኝ።

## የጌድዮንና የሄኖክ መወለድ

ግንቦት 10 ቀን 1956 ዓ ም ጧት ከመኝታዬ ስነሳ ሌሊት ያየሁት መጥፎ ህልም ትዝታ እየረበሸኝ ነበር፡፡ ህልሙ የፈጠረብኝን ስሜት ስግደይ አካፈልኳት፤ እኔም መጥፎ ህልም እይቼ ነበር አለችኝ፡፡ እከታትላም ሌሊት ደም እንደ ፈሰሳት ነግረችኝ፡፡ የህክምና እውቀት ስላላት "የዚህ ደም መታየት የምን ምልከት ነው?" ብዬ ሳጋት ባዘለ ድምጽ ጠየኳት፡፡ "ጥሩ ምልከት አይደለም" ነበር መልሷ፡፡ እቅዳችን አማኑኤልና ሩትን ባዋለደጂት ዶከተሮች እጅ በናዝሬት ሄዳ እንድትወልድ ነበር፡፡ በሁኔታው ልቤ በጣም ተረበሸ፡፡ ገና ማለዳ ጠዋት ስለ ነበር ወደ አንዲት ከፍል ገብቼ በግንባሬ ተደፍቼ፣ "ጌታ ሆይ! ምን ሊመጣብን

ነው?" በማለት በጸሎት መንፈስ ቆዘምኩ፤ ወዲያው ልቤን የሞላው ሃሳብ፡ - ሮሜ 8፡28 "እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚሆን እናውቃለን" የሚለው ነበር። ከጸሎት ስነሳ "በእኔ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ነገር ለእኔ ጥቅም ወይም ለጌታ ክብር ነው፤ ለሁሉቱም ተዘጋጅቼአለሁ" ብዬ ቀኑን ለእግዚአብሔር ሰጥቼ፡ ቁርሴን በልቼ ወደ ሥራዬ ሄድሁ።

ረፋድ ሲል ግደይ እኔን ፍለጋ ወደ ት/ቤት መጣች። ክፍል በማስተማር ላይ ስለ ነበርኩ አቶ ይፍሩ ገበየሁ መኪና አዞላት ወደ ሆስፒታል ተወሰደች። ሹፌሩ ሲመለሱ አልጋ ይዛ መተኛቷንና ከቤት እንዲመጣላት ምትፈልግውን እቃ ዝርዝር ነገሩኝ፤ ወዲያው ይዤላት ሄድሁ። ተመቻችታ ተኝታ አገኘኋት። አረፍ ማለቷን ሳስብ "ማታ እመጣለሁ" ብዬ ወደ ቤት ተመለስኩ።

ወደ ማታ ላይ ተመልሼ ስሄድ ክፍሏ ዉስጥ የለችም። የሠራተኞች ፈረቃ የሚለወጥበት ሰዓት ስለነበር ወደ ነርሶች ቢሮ ሄጄ "ቁጥር 2 ተኝታ የነበረችው ወዴት ሄደች?" ብዬ ስጠይቅ "ወደ ቤት ሄዳለች አሉኝ" ግራ ገባኝ። ሊሆን አይችልም ብዬ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል አካባቢ ሄድኩ። ዶክተሩ በሩን ከፈት ሲያደርግ አየት አደረገኝና "ወንድ ልጅ ገላግለናታል" ብሎ በሩን ዘግቶ ተመለሰ። የጌዴዎንን መወለድ እንዲህ ባለ ሁኔታ ነበር የሰማሁት።

በ1957 ዓ.ም በምክትል ዲሬክተርነትና የትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆኜ መስራቴን ቀጠልኩ። ህፃኑ ጌዲዮንም በማደግ ላይ ነበር። ሁላችንም ደስተኞች ነበርን። የቤታችንን ደስታ የሚያደፈርስ ችግር በጌዲዮን ላይ ማስተዋል ጀመርን። ጌዲዮን እንደ በፊቱ ጭናችን ላይ ቆሞ መጫወት አያቃተው፣ ቀኝ እግሩ እሱን ተሸከማ መቆም እያቃታት ዝልፍልፍ ማለት ጀመረች። ደጋግመን በተለያየ መንገድ ለማቆም ሞከርን ውጤቱ ተመሣሣይ ነበር። እግሩ ጠንክራ መቆም አትችልም ተዝለፍልፋለች። ደነገጥን፣ ምንሆኖ እንደሆነ ማወቅ ስላልቻልን ተረበሽን። ወደ ሆስፒታል ወሰድነው። ዶክተሩ "ፖሊዮ ነው" አለን፤ "ፖሊዮ?!" የበለጠ ግራ ገባኝ ፖሊዮ ምን እንደሆነ አላውቅም። ግደይ ለቅሶዋን ለቀቀችው።





"መድኃኒት የለውም እግሩ እንዲጠነክር አሻሹለት፤ መታጠቢያ ገንዳ ዉስጥ ውኃ ሞልታችሁ እንዲንላፈፍና እግሩን እንዲያንቀሳቅስ ኮርኩሩት፤ ፍል ውኃ ያለበት ቦታ ውሰዱት" አለን።

በጣም አዝነን ወደ ቤታችን ተመለስን። በቤታችን መታጠቢያ ገንዳ የለንም፤ ያለን ሻወር ነው። ገንዳ እንዴት ማግኘት እንደምችል አሰብኩኝ፤ ወደ እንጨት ቴክኖሎጂ ክፍል ሄጄ ትልቅ የእንጨት ገንዳ አሰራሁ። ወደ ብረታ ብረት ክፍል ሄጄ ይጥና በየነን በቆርቆሮ እንዲለብደውና ውኃ መያዝ እንዲችል በሶልደር (የሚቀልጥ ብረት)እንዲያያዝ እስደረግኩ። በትልቅ ብረት ድስት ውኃ እያሞቅን ገንዳውን ሞልተን እዚያ ዉስጥ እንዲንቦራጨቅ አደረግን። የምንችለውን ሁሉ ማድረጋችን ጥቂት የህሊና እረፍት ቢሰጠንም የጌዲዮን ፈጽሞ አለመዳን ግን ያስጨንቀን ነበር። በዚያን ጊዜ ግደይ ሄኖክን ነፍሰ ጡር ነበረች። የመውለጃዋ ቀን ሲቃረብ ወደ ናዝሬት ሄዳ እንድትወልድ ቅድመ ዝግጅታችንን ጨርሰን ሄደች። ሰኔ 24 ቀን 1957 ዓ.ም በዶክተር ሸርነር ከራትዝ እጅ ሄኖክን ተገላገለች። አራተኛ ልጅ!

## የስንብት ጥያቄ

ከሄኖክ መወለድ በኋላ ብዙም ሳልቆይ የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ጽፌ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር የሁለተኛ ደረጃና የሙያ ት/ቤቶች ዋና ዲሬክተር አቶ ኃይለ ሚካኤል ምስግና ጋር ቀረብኩ። ደብዳቤዬ አጭር ነበረች።

"ትምህርት ሚኒስቴር አስተምሮኛል፣ ለከፍተኛ ትምህርትም ወደ ዉጭ አገር ልኮኛል፣ የመጀመሪያ ሥራ ቀጣሪዬም ነው (በ48 ዓ.ም ከተግባረ ዕድ እንደወጣሁ በአስተማሪነት እዛው መቀጠሬን መጥቀሴ ነው) ስለዚህ ሁሉ በጣም እያመሰገንሁ ከሥራ እንዲያሰናብተኝ በማክበር አመለክታለሁ"።

ደብዳቤውን ስሰጣቸው እንደ መደንገጥ አሉና "ምነው ከይፍሩ ጋር ተጣላችሁ እንዴ?" አሉኝ። "የለም አልተጣላንም" አልኳቸው። "ታዲያ ለምን ልትለቅ

ፈለግህ?":: ደጋግሜ ያሰብኩበትን ጥያቄ ነበር የጠየቁኝ:: ከመናገሬ በፊት ጊዜ ወሰድኩ:: ሁለት ምክንያቶች ነበሩኝ ባሕር ዳርን እንድለቅ የገፋፉኝ:: ምንም ሳልደብቅ ሁለቱንም ነገርኳቸው::

"እንደሚያውቁት የልጄ የጌዴዎን ጤንነት ያሳሰበኛል:: ለእርሱ የተሻለ የህክምናና የፍል ውኃ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መሃል አገር ጠጋ ማለት ይገባናል:: በተጨማሪ እንደሚያውቁት የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አማኝ ነኝ:: የቤተክርስቲያኔም ሊቀ መንበር ነኝ:: የመሪዎች ስብሰባ የምናደርገው በእረፍት ጊዜዬ ነው:: በአሁኑ ጊዜ የሜኖናይት ሚሲዮን የትምህርትና የህክምና አገልግሎቱን ለአገሬው ሰዎች እያዳረሰ ነው:: እኔም የዚህ አገልግሎት ተካፋይ እንድሆን በተደጋጋሚ ጥሪ ቀርቦልኛል:: ከወንጌላውያን አማኝ ወገኖቼ ጋር በመሆን የምንወዳት አገራችንን በጤናና በትምህርት ረገድ የሚጠበቅብኝን ለማድረግ እፈልጋለሁ:: ለቤተክርስቲያኔ ጥሪ ምላሽ መስጠት እፈልጋለሁ" አልኳቸው::

በጥሞና ካዳመጡኝ በኋላ "ጌዲዮን አሁን እንዴት ነው?" ፊታቸው ላይ ሃዘኔታ አነበብኩ:: "ደህና ነው ቢሆንም ግን የተሻለ ሕክምና ማግኘት አለበት፤ ለዚህ ደግሞ ወደ መሐል አገር መምጣት አስፈላጊ ነው" አልኳቸው በድጋሜ። ቀጠል አድርገው "ሚሲዮኑ የሕክምናና ትምህርት አገልግሎት የት አካባቢ ነው የሚሰጠው?" አሉኝ እንደማሰብ ብለው:: "አብዛኛው አገልግሎታችን ናዝሬት አካባቢ ነው፤ ሐረር ጠቅላይ ግዛትም አለን" አልኳቸው። "ልናሰናብትህ አንፈልግም፤" አሉኝ:: ደንገጥ አልኩ አንለቅህም ሊሉኝ ነው እንዴ ብዬ በሆዴ አሰብኩ:: ጥቂት ዝም ብለው ቆይተው "በዚያው አካባቢ ዳሬክተር ብናደርግህስ?" አሉኝ:: "ለምሳሌ የት?" አልኩ በፍጥነት:: "ለምሣሌ ሐረር መድሃኔ ዓለም፣ ደብረ ብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ፣ አዲስ አበባ ምንሊክ ት/ቤት፣ ናዝሬት አጼ ገላውድዮስ" አሉኝ። ናዝሬት አጼ ገላውድዮስን መረጥኩ:: እርሳቸውም ደስ አላቸው የዝውውርና የሹመት ደብዳቤውን በማግሥቱ መጥቼ እንድወስድ ነግረውኝ ወጣሁ።





የሹመት ደብዳቤው ከሐምሌ 21/1957 ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ይላል:: አንድ ወር ያህል ጊዜ ነበረኝ ስለዚህ ወደ ፖሊቴክኒክ ተመልሼ፣ የጀመርኩትን የሚቀጥለውን አመት የጊዜ ሰሌዳ፣ የተማሪዎች የመምህራን ሥራ ድልድል ጨረስኩ:: እቃችንን በፖሊቴክኒክ የጭነት መኪና ጭነን ባሕር ዳርን ለቀን ወደና ዝሬት አቀናን::

## የአፄ ገላውዲዮስ ት/ቤት ዲሬክተርነት፣ አገልግሎት በናዝሬት

ናዝሬት እንደገባን በጥቂት ቀናት ውስጥ የአጼ ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ከነበረው ጎበጻዊው ሥራዬን ተረከብሁ:: ፊጥኜ እራሴንና ትምህርት ቤቱን ማዘጋጀት ጀመርሁ:: አንደኛው ዝግጅቴ ከአቶ ተገኔ ከሚባሉ የአውራጃው ት/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ጋር መለማመድ ነበር::

ትምህርት ቤቱ ምንም ልዩ በጀት አልነበረውም:: የተሰበሩ ወንበሮችን ለመጠገንና ለማጸዳዳት አቶ ተገኔን ገንዘብ ብጠይቅ ምንም በጀት እንደ ሌለ ነገሩኝ:: የቀድሞው ዲሬክተር የተማሪዎችን እጅ ስራ ውጤቶች ሽያጭ ገንዘብ ለእርሳቸው እንዳስረከብ ሰጥቶኝ ነበር:: እኔ ግን ለአቶ ተገኔ በማስረከብ ፈንታ ለተሰበሩ መቀመጫዎች መጠገኛ የሚሆኑ ምስምሮችና ኮላዎች ገዛሁበት:: ይህም እርምጃዬ በእኔና በአቶ ተገኔ መካከል የአሠራር ግጭት ጫረ::

ጥቂት ቆይቶ ብዙ ተማሪዎች እንድቀበል የሚያዝ ወረቀት ደረሰኝ:: አብዛኞቹ ወንበሮች ስለተሰባበሩ ባለው አግዳሚ ወንበር መቀበል ከባድ ነበር:: ወንበሮች ትንሽ እንደሆኑና ባዶ ክፍሎች እንዳሉ በመግለጽ ወንበር እንዲሰጠኝ አመለከትኩ:: ሸዋ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት አመልከት ተባልሁ:: ወደእዚያ ሄጄ የተማሪዎች መቀመጫ ካልሰጣችሁኝ ተማሪ መቀበል አልችልም በማለት አመለከትኩ:: ታላቅ ተግዳሮት ነበር:: ቢሆንም ይሰጥሃል ተባልሁ::

ወደ ናዝሬት ዲሬክተር ሆኜ ልዘዋወር መሆኑን ሲያውቁ ብዙ ሰዎች እነ አሰራት ገብሬ ጨምሮ "የናዝሬትን ተማሪዎች አትችላቸውም " በማለት አስፈራርተውኝ

ነበር፡፡ ባልፈራም ግን በቂ ዝግጅት ማድረግ ነበረብኝ፡፡

መስከረም መጀመሪያ ላይ የመምህራን ስብሰባ ጠራሁ፤ በዚያ ስብሰባ ላይ ስለተማሪዎች ዲሲፕሊን ያለኝን እቅድ ገለጽኩላቸው፤ ሰፊ ውይይት አደረግን፡፡ በዉይይቱ ላይ አንድ ነባር ሐንዳዊ መምህር ብድግ ብሎ፣ ተማሪዎቹ በጣም አስቸጋሪ እንድሆኑ በሃይለ ቃል ገለጸ፤ እንዲህ በማለት፡-

"መምህራንን አያከብሩም፣ የሚነገራቸውን አይሰሙም፤ አክብሮት የማያውቁ፣ ባለጌና መረን ናቸው"፡፡ የአገሬ ወጣቶች በውጭ አስተማሪ እንዲህ ሲተቹ መስማት በእውነቱ አሳዘነኝ፡፡

እኔም ፍርጥም ብዬ፡- "ተማሪዎች የሚያንጸባርቁት ባህርይ እኛ እንዲሆኑ የምንፈቅድላቸውን ዓይነት ነው፡፡ ሁላችንም በድስፕሊን ጉዳይ አንድ አቋም ከኖረን ጋጠ ወጥነታቸው ይገታል፡፡ ከዚህ በኋላ ተማሪዎች ሲያጠፉ ማስታወሻ ጽፋችሁ ላኩልኝ፤ የመጀመሪው ወር ላይ ብዙ ማስታወሻዎች ሊላኩ እንደሚችሉ አስባለሁ፤ እኔ እንደ አግባባቸው እስተናግዳቸዋለሁ፡፡

አንድ ነገር እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ፤ ያም እንደምተማመንባችሁ ነው። አስተማሪና ተማሪ ተካሳችሁ ቢሮዬ ብትመጡ አቋሜ አስተማሪው ልክ ነው ብዬ ነው የማምነው፡፡ እንደ እምነቴ ግን እንድትሆኑ እጠብቃለሁ፡፡ ብቃታችሁን ልታሳዩኝ ይገባል" አልኳቸው፡፡

ትምህርት ተጀመረ፤ የመጀመሪያው ሳምንት የሰርአት ማስከበር መማሪያ ጊዜ ነበር። ተማሪ በሰአቱ ክፍል መግባት አለበት፡፡ እርፋጅ ተማሪና ክፍል ውስጥ የሚረብሽ ተማሪ ወደ እኔ ይላካል፡፡

በተማሪዎቹ ረብሻ የተማረረው ሐንዳዊ መምህር ዘጠኝ ተማሪዎች ይዞ ወደ ቢሮዬ በመምጣት ጥፋታቸውን ነግሮኝ ወጣ፡፡ የእያንዳንዱን ስም ከተሰጠኝ ዝርዝር ጋር ለማመሣከር መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ አንዱ እጁን ኪሱ ዉስጥ አድርጎ እየተንጠባረረ ስሙን ነገረኝ፤ ያባቱን ስም ስጠይቀው እንደዛው እንደተንጠባረረ መለሰልኝ፡፡ ከመቀመጫዬ ተነስቼ ፊቱ ቆምኩ፤ ባላሰበውና ባልጠበቀው ሁኔታ





በጥፊ አጠናገርኩት፡፡ ቁጣ ባዘለ ድምጽ "የምታናግረው ጃንሆይ እዚህ ወንበር ላይ ያስቀመጡትን ሰው ነው" ብዬው ተቀመጥሁ፡፡ የቀሩትን መዝግቤ ከዚህ በኋላ በምንም ምክንያት እኔ ጋር ተከሰው ቢመጡ ወላጅ ይዘው እንዲመጡ ነገሬ አሰናበትኳቸው፡፡ የዛን ቀን በጡበራራው ልጅ የደረሰው ነገር በመላ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ተሰማ፡፡ የተማሪዎቹ ረብሻ ቀስ በቀስ እየቀነሰና እየረገበ መጣ፡፡

እጬ ገላውድዮስ ት/ቤት የዲሬክተርነት ስራዬን እየሰራሁ በናዝሬት መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጀመርሁ። በዚያን ጊዜ የመጀመሪያው የመሰረተ ክርስቶስ መጋቢ ሆኜ ተካንኩ፡፡ በተካንሁበት ቀን መልእክት ያቀረበው ፖል ጊንግሪክ ነበር፤ በመልእክቱ መሐል ለሕይወት ዘመኔ የቀረልኝን ነገር ተናገረ፡፡ "የዛሬው ቀን ለመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ቀን ነው፤ ሚሊዮንም ታላቅ ክብር ሊሰማው ይገባል፤ ነገር ግን <u>ለእያንዳንዱ አንድ ግራም ክብር አንድ ኪሎ ኃላፊነት አለበት" አለ</u>። ይህ አባባሉ በቀጣይ ዘመን አገልግሎቴና ህይወቴ ውስጥ ሁሉ ሳስታውሰው ኖሬያለሁ፡፡

## የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ድሬክተርነት

በእጬ ገላውዲዮስ የዲይሬክተርነት ሥራዬ መስመር ይዞ፣ ናዝሬት መሠረተ ክርሰቶስም ማገልገል እንደ ጀመርኩ ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ ወደ ትምህርት ምኒስቴር ከግደይ ጋር እንድንቀርብ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ "እኔስ እሽ ግደይ ደግሞ ለምን ተፈለገች?!" መልስ የሚሰጠኝ አላገኘሁም፡፡ ግደይ በወቅቱ የናዝሬቱን ቤታችንን ቀለም እየቀባባች፣ መጋረጃ ሰፍታ እየሰቀለች፣ በማስማመር ስራ ተወጥራ ነበር፡፡ የናዝሬት ኑሯችን ተመችቷታል፡፡ በተለይ የጌዲዮንን ጤንነት ለመከታተል ስለ ተመቻት ከሁሉ በላይ አስደስቷት ነበር፡፡ ቤት እንደገባሁ ስለ ጥሪው ነገርኳት፡፡

የጠሩን አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ነበሩ፤ (አቶ ተድላ ግደይንም ያውቋታል፤ ግደይ ሩትን ልትወልድ ስትል ከመቀሌ ይዘዋት የመጡት እሳቸው ነበሩ)፡፡ "ዛሬ

ወ/ሮ ግደይን ይዘህ እድትመጣ ያደረግነው ሁለታችሁንም የምንጠይቀው ብርቱ ጉዳይ ስላለን ነው፤ በተጨማሪም ብቻህን ብናነጋግርህ ከአርሷ ልማከር ማለትህ እንደ ማይቀር ስለተረዳን ነው":: "ምን ብርቱ ጉዳይ ይሆን?!" የማወቅ ጉጉቴ ጨመረ:: "ባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ እንድትመለሱ እንፈልጋለን" አሉን:: ቀድማ መልስ የሰጠቹው ግደይ ነበረች፤ "እይ! ይሄ የሚሆን ነገር አይደለም" ስትል:: በትህትና ለመናገር ብትሞክርም ለመመለስ ፍጹም ፈቃደኛ አለመሆኗ ድምጿ የበለጠ ያረጋግጥ ነበር:: ሌላው ሁሉ ይቅርና ለልጃችን ለጌዴዎን የተሻለ የህክምና እርዳታ ከምናገኝበት አካባቢ መራቅ አስቸጋሪ መሆኑን አጥብቃ ለመስረዳት ሞከረች:: አቶ ተድላ ግደይን ለማሳመን ጥረታቸውን ቀጠሉ:: እኔ ግን ስለ ሁኔታው አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቤ ሁስቱንም አመለከት ነበር:: በመጨረሻ ግን በብዙ ልምምጥ እሺ አሰኙዋት::

ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች የሰው ኃይል የሚሰለጠንበት ዋና ት/ቤት ነው:: እንዲህ ያለ ሥልጠና አዲስ ካለሙትና ካቀዱት መምህራን አንዱ ነኝ:: ወጣቶችን በቴክኒክ ሙያ ማሰልጠን በጣም የምወደው ስራ ነው:: አሜሪካ ድረስ ሄጄ የሰለጠንኩትም ለዚሁ ነው። ወደ ናዝሬት ከመምጣቴ በፊት በአዲስ መነሳሳት ትምህርቱን እመራ ነበር ደስተኛም ነበርኩ:: እኔም ወደ ባህርዳር መመለሱን ተቀበልኩት:: የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ለመሆን እቃዬን ጭኘ ወደ ባህር ዳር ተመለስን።

በመጀመሪያው አመት የዳይሬክተርነት ዘመኔ ከአንድኛና ሁለተኛ አመት ተማሪዎች ጥያቄ ቀረበልኝ:: "እኛ ወደ ፖሊቴክኒክ የመጣነው ከአስረኛ ክፍል ሲሆን ሶስተኛ አመት ተማሪዎች የመጡት ከስምንተኛ ክፍል ነው፤ ታዲያ ስንመረቅ ምን የሚባል ወረቀት ነው የሚሰጠን?" የሚል ነበር። እያሰቡ ያሰውን ስምቼአለሁ። እንዳልሰማ ምን መባል አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ አልኳቸው። "ከአስረኛ የመጣነው ዲፕሎማ ይባል የእነርሱ ከስምንተኛ ክፍል የመጡት ደግሞ ሰርቲፊኬት መባል አለበት" አሉ:: ለአቤቱታቸው ምላሽ ስሰጥ "የሚሰጣችሁ ወረቀት መባል ያለበትን የሚወስነው ትምህርት ሚኒስቴር ነው"





አልኳቸው:: ተማሪዎቹም "ትምህርት ሚኒስቴር የእናንተን ጥቆማ መሠረት አድርጎ ነው የሚሰጠን አሉ።" ብዙ ተነታረክን፤ በመጨረሻ ፤ "የናንተ ኃላፊነት ጸጥ ብሎ መማር ነው፤ የሚሰጣችሁ ሰርቲፊኬት ይሁን ወይንም ዲፕሎም በኋላ የሚወሰን ይሆናል" አልኳቸው:: ተማሪዎቹም "የስምንተኛ ክፍሎች ሰርቲፊኬት የእኛ ዲፕሎም መባል አለበት፤ ይህ የማይሆን ከሆነ ትምህርት ቤቱን ለቀን እንወጣለን" አሉኝ:: "በሩ ያውላችሁ" አልኳቸው። "ውጡ ነው የምትሰን?" ብለው አከርረው ጠየቁ። በድጋሚ "ጸጥ ብላችሁ የማትማሩ ከሆነ በሩ ያውላችሁ" አልኳቸው።

ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ሄደው አቤት አሉ:: ንትርኩ ቀጠለ፤ አገረ ገዢው መጥተው መከሩዋቸው፤ እምቢ ሲሉ፣ ለትምህርት ሚኒስቴር እነግርላችኋለሁ ብለው ሄዱ። አገረ ገዢው ብቻ ሳይሆን እኔም አሳውቄ ስለነበር የት/ሚኒስቴር ባለስልጣናት መጡ:: የመጡት ባለስልጣናት የቀድሞው የፖሊቴክኒክ ዲሬክተር አቶ ይፍሩ ገበየሁና የንግድ ት/ቤት ዲሬክተር የነበሩት አቶ ሰይፉ ዘለቀ ነበሩ። (አቶ ሰይፉ ዘለቀ የሐረር ጠቅላይ ግዛት ት/ቤቶች ኢኒስፔክተር በነበሩበት ጊዜ እኔን ስምንተኛ ክፍል እንድፈተን ያደረጉ ሰው ናቸው፤ በዚህ ወቅት ነበር እንዴት እንድንፈተን እንዳደረጉ ዝርዝሩን የነገሩኝ)።

ረዥሙን የአድማ ታሪክ ስናሳጥረው ባለስልጣናቱም የእኔን ዉሳኔ አጸደቁ። ተማሪዎቹ "እንወጣለን" አሉ። "ልትወጡ ትችላላችሁ፤ ሆኖም ከዚህ ወጥታችሁ የምትገቡበት ት/ቤት የለም" አሉዋቸው:: አሻፈረን አሉ:: እቃቸውን እስረከበው ወጡ፤ በመጀመሪያው ቀን እዚያው ከተማ አይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ አደሩ፤ በሚቀጥለው ቀን 5 ኪሎ ሜትር ላይ ሰፍረው አደሩ። የባሕር ዳር ከተማ ሽማግሌዎች እካሄዳቸው እንደማያዋጣቸው ያሉበት ድረስ በመሄድ መከሩዋቸው:: ከባሕር ዳር ሳይወጡ ቢመለሱ እንድቀበላቸው ተማጸኑኝ፤ እኔም በሁለት ቀን ዉስጥ የሚመለሰን ተማሪ እንድምቀበል ገለጽሁ፤ በማግሥቱ ሁሉም ከንፏን አንደ ተመታች አሞራ ሆነው ተመለሱ፤ ተቀበልኳቸው። በሚቀጥሉት ቀናት ያንን አድማ መሩ የምንላቸውን 12 ተማሪዎች አባረርን::

ይህ በመጀመሪያው ዓመት የዲሬክተርነት ዘመኔ ከተማሪዎች የገጠመኝ ተግዳሮት ቢሆንም በአስተዳደርም በኩል ችግር አጋጥሞኝ ነበር፡፡ አዳሪ ት/ቤት እንደ መሆኑ መጠን ብዙ ገንዘብ ለተማሪዎች ምግብ ወጪ ይደረጋል፡፡ ተጋዛ የሚባለው የምግብ አይነት ደረሰኝ ከሞዴል 6 ጋር ተያይዞ ወጪውን እንዳጸድቅ ይቀርብልኛል፤ ከዚያም በወጪነት ይመዘገባል፤ ምግብ ተገዛ ተብሎ ብዙ ደረሰኝ ይቀርብልኛል፤ ያን ደረሰኝ ስፈርምበት ገንዘቡ በወጪነት ይመዘገባል። በዚህ መልኩ የሚወጣው ገንዘብ ብዙ ነው፤ አላማረኝም፤ እንዴት ልቆጣጠረው? ተጨነኩ፡፡ አውጥቼ አውርጄ በመጨረሻ "ምግብ የሚገዛው በጨረታ ነው" አልኩ፡፡ የምግብ አይነቶችን ዝርዝር አሰወጣሁና "እነኚህን ምግቦች ት/ቤቱ በሚፈልገው መጠን እስከ ሰኔ 30 የሚያቀርብ ነጋዴ፣ በኪሎ/በቁጥር ምን ያህል እንደሚጠይቅ ዋጋ ያቅርብ" አልኩ፡፡ ነጋዴው የሚሰጠው ዋጋ የሚያገለግለው ለአንድ አመት ነበር፡፡ የምግብ ዋጋ በየጊዜው ተለዋዋጭ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ የሽንኩርትና የድንች ዋጋ በተለያየ ጊዜ ብዙ የዋጋ ልዩነት ያሳይ ነበር፡፡ ነጋዴው ይህን ሁሉ ከግምት በማስገባት ነበር የሚያዋጣውን ገንዘብ የሚሰጠው፡፡

አንድ ቀን አስተዳዳሪ እንዲሆነኝ የተሰጠኝ ሰው ወደ ቢሮዬ መጣና፡ "አቶ ሚሊዮን፤ በአሁን ጊዜ ድንች አንዱን ጆንያ በሰምንት ብር ልንገዛ እንችላለን፤ ለምን አስራ ሰድስት ብር እንከፍላለን" አለኝ። "ድንች አሁን ረከሶ ሊሆን ይችላል ነገር ግን የሚወደድበትም ጊዜ አለ፤ ይህንን ሁሉ አገናዝበ ነው የጨረታው ዋጋ የተሰጠው" አልኩት፡፡ መልሴ አልተዋጠለትም። እንዲያውም ነጋዴውን እንደረዳሁት ቆጠረ፡፡ ይህንና ሌሎችንም ነገሮች ጨማምሮ ትምህርት ሚኒስስቴር ከሰሰኝ። ከትምህርት ሚኒስቴር ሰዎች መጥተው ጉዳዩን አጣርተው ሄዱ። ጥቂት ቆይቶ አስተዳዳሪው ከአዛ ተነሳ።

ፖሊን ማስተዳደር ቀላል አልነበረም፡፡ አዳሪ ት/ቤት እንደ መሆኑ ተማሪዎች በአእምሮም ሆነ በስጋ ለሚመገቡት ጉዳዮች ሃላፊው እኔ ነበርኩ፡፡ ግንኙነቴ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ብቻ አልነበረም። ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋርም ነበር። ለፖሊ. ልዩ ልዩ ከፍሎች የተመደበ በጀት ነበረኝ፤ ገንዘቡን የማገኘው ከገንዘብ





ሚኒስቴር ነው፤ በአመቱ መጨረሻ በተመደበው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት ይመለሳል፡፡ አመቱ ከማለቁ በፊት የማንጠቀምበትን ምክንያት ገልጬ ወደ ሌላ እንዲዘዋወርልን ገንዘብ ሚኒስቴርን አጠይቅና ይፈቀድልኛል፡፡ እንዲህ ያለው አጋጣሚ የኢትዮጵያን መንግሥት ገንዘብ አወጣጥና አያያዝ እንዳውቅ አደረገኝ። ከአቶ ቡልቻ ደመቅሳ ጋር የተዋወቅሁት ያኔ ነበር። ያኔ እርሳቸው የገንዘብ ምኒስቴር ምክትል ምኒስትር ነበሩ።

ፖሊን ማስተዳደር ቀጥዬ የመጀመሪያዎቹ ምሩቃን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ዲፕሎማቸውን እንዲቀበሉ አደረግሁ፡፡ እለቱ በሕይወቴ ካጋጠሙኝ ታላቅ ቀናት አንዱ ነበር፡፡ አባቴ አቶ በለጠ ወልደገብርኤል በበአሉ ላይ ለመገኘት ከሃሪርቲ መጥቷል፡፡ እኔ ልጁ ለግማሽ ቀን ያህል የንጉሥ ባለሟል ሆኜ መዋሌን ማየቱ ታላቅ ደስታና ኩራት ፈጥሮለት ነበር።

በእለቱ ጃንሆይ ግቢ እንደገቡ የተቀበሉዋቸው የትምህርት ምኒስትሩ ክቡር አቶ አካለ ወርቅ ወልደ ኪዳን ነበሩ፡፡ ጃንሆይ ከመኪናቸው እንደ ወረዱ እጅ ከነሱ በኋላ ወደ እኔ ዞር ብለው ከጃንሆይ ጋር አስተዋወቁኝ፡፡ እኔም ለጥ ብዬ



ጃንሆይን ለመጀመሪያዎቹ የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ተመራቂዎች ዲፕሎማ ሊሰጡ በመጡበት ወቅት ግቢውን እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ

እጅ ነሳሁ፡፡ ጃንሆይ ዲፕሎማ ከመስጠታቸው በፊት ተመራቂ ተማሪዎች የተማሩትንና የሰሯቸውን ስራዎች ፖሊቴክኒክን እያዞርሁ ለሁለት ሰዓት ያህል አስጎበኘኋቸው፡፡

ግርማዊነታቸው ትልቁ አዳራሽ ገብተው በተዘጋጀላቸው ዙፋን ላይ ተቀመጡ። ከአርሳቸው ፊት እንግዶችና ተማሪዎች ተቀመጡ፡፡ የትምህርት ሚኒስቴሩ ስለ ጎጃም ጠቅላይ ግዛት የትምህርት ሂደት ንግግር አደረጉ፤ ቀጥሎ እኔ ስለ



ጃንሆይን ፖሊቴክኒክን ሳስጎበኝ



ጃንሆይ እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ









ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ትምህርት አሰጣጥ ባጭሩ መግለጫ ከሰጠሁ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ምሩቃን ዲፕሎማ እንዲሰጡልኝ 150 ተመራቂዎች ማቅረቤን ገለጽሁ፡፡

ቀጥሎ ግርማዊነታቸው በመላው አገር በመሰጠት ላይ ስላለው የትምህርት ፕሮግራምና ስለምኞታቸው ንግግር አድርገው፣ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ይህን ት/ቤት እንድናቋቁም ስላደርጉት አስተዋጽዖ አመስግነው በዚያች ቀን ለመጀመሪያዎቹ ምሩቃን ዲፕሎማ ለመስጠት በመምጣታቸው ደስ መሰኘታቸውን ገልፀው ንግግራቸውን ጨረሱ፡፡ በመጨረሻም እኔ የተመራቂዎቹን ስም እየጠራሁ ዲፕሎማቸውን እንዲቀበሉ አደረግሁ፡፡

ለሁሉም ተማሪዎች ዲፕሎም ከተሰጠና ከየክፍሉ ጥሩ ዉጤት ያገኙ ከተሸለሙ በኋላ ታላቅ የምሳ ግብዣ ተደረገ። በመጀመሪያ ግርማዊነታቸውና እንግዶች ቀጥሎ መላው ተማሪዎች ተመገቡ። የት/ቤቱ ወጥ ቤት ሃላፊ ግደይ ነበረች። ከቤተ መንግሥት ከመጡት የምግብ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የንጉሡን ምግብ የማዘጋጀት እድል በማግኘቷ ቀኑ ለእርሷም ልዩ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ በግርማዊነታቸው ስም ለባሕር ዳር ሹማምንትና ያገር ሽማግሌዎች ግብር ቀረበ። ግርማዊነታቸው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ሲሄዱ እኔ እልጋወራሽን ወደ አዲስ አበባ ሸኝቼ ለመሰስ ነበር በጣም እንደራበኝ የተገነዘብኩት፡፡ በእኔ አስተዳደር ስር ብዙ ሰዎች የተጋበዙበትና የጠገቡበት ቀን ቢሆንም እኔ ግን የተራብኩበት ቀን ሆነ፡፡ ራስ ሆቴል ጎራ ብዬ ምሳዬን በልቼ ረሃቤን አስታገስኩ።

በቀጣዮቹ ወራት ለተመረቁት ሥራ ማፈላለግ ጀመርን፡፡ በፖሊቴክኒክ ረዳት አስተማሪዎች እንዲሆኑ ከፍተኛ ዉጤት ያገኙትን መርጠን አስቀረን፡፡ ከመላው ኢትዮጵያ ካሉ ኩባንያዎች በቀረበልን ጥያቄ መሠረት ምሩቃንን መመደብ ቀጠልን፡፡ አንድ ቀን ከትምህርት ሚኒስቴር አቶ ተድላ ዘዮሃንስ ደውለው "የሩስያ መንግስት ለ17 ምሩቃን ሙሉ ስኮላርሺፕ ስለ ሰጠ፣ ከመምህራን ልዩ ኮሚቴ አቋቁመህ 17 መርጠህ ስማቸውን እንድትልክ" አሉኝ። በታዘዝኩት መሠረት 17 አስመርጬ/መርጬ ወደ ቢሮዬ እንዲመጡ አስደርጌ የምስራቹን

ነገርኳቸው፡፡ ደስ እያሰኘ "መልካም እድል ነው ያጋጠማችሁ፤ ሙሉ ስኮላርሺፕ ነው ያገኛችሁት፤ እዚህ በተማራችሁት ላይ በተጨማሪ ሥልጥናችሁ መጥታችሁ አገራችሁን በሚገባ ለማገልገል ትችላላችሁ፤ እንግዲህ አሺታችሁን እያንዳንዳችሁ በየግላችሁ፣ በዚህ ሳምንት ዉስጥ መጥታችሁ እንድታሳውቁኝ" አልኳቸው።

ምላሻቸው አስገረመኝ፡፡ እድሉ ከተሰጣቸው አስራ ሰባት ተማሪዎች ለመሄድ የተስማሙት ሰምንት ብቻ ነበሩ፡፡ እድሉ እንዳይታጣ በማጣሪያ የተውናቸውን ተማሪዎች ጋበዝኳቸው፤ አሁንም አራት ተማሪዎች ብቻ ነበሩ አሺታቸውን የሰጡት፡፡ በጠቅላላው አስራ ሁለት ብቻ አገኘሁ፤ ቀሪውን ኮታ ለመሙላት በረዳትነት ለሚሰሩት እንደ አቶ ማንደፍሮ ላሉት ስጠሁና ይህንኑ ለትምህርት ሚኒስቴር ገለጽሁ፡፡ የተማሪዎቹ ለመሄድ አለመፈለግ እኔን ብቻ አልነበረም ያስገረመኝ፤ እዚያ በማስተማር ላይ ያሉት መስኮባውያን መምህራንም በጣም ተገርመው ነበር፡፡

## የባሕር ዳር መንፈሳዊ አገልግሎት

ባሕርዳር እንደገባሁ ከኃ.ማ.ማ.መ. ሆስፒታል የድሬስርና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ምሩቅ የሆነ፣ መድሃኒት ቤት ከፍቶ የሚኖር ወንድም አገኘሁ፡፡ መቀሌ እንዳደረግሁት ቤት ተከራይተን የጸሎት ቤት እንከፈት አልኩት፡፡ "ለጸሎት ቤት የሚሆን ቤት አይገኝም፤ ከዚህም በላይ እንደዚህ ያለ ነገር እዚህ ጎጃም አይታሰብም" አለኝ፡፡ ስለዚህም ከእርሱና ከጥቂት ተማሪዎች ጋር በቤታችን አምልኮ ጀመርን፡፡ አምልኮአችንን የቀድሞ መዝሙሮችን በመዘመር እንጀምር ነበር፡፡ ከመዝሙሮቹ አንዱ "የሱስ ሆይ . ." የሚለው ነበር።

የሱስ ሆይ አትለፍብኝ፡ ጸሎቴን ስማ
ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ አትለፍብኝ
የሱስ ክርስቶስ ጸሎቴን ስማ





ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ፡ አትለፍብኝ

አሁን ወደ ጸጋህ ዙፋን እመጣለሁ
ይቅርታህን ለመቀበል እርዳኝ አቤቱ
የሱስ ክርስቶስ . ..

ስለቸርነትህ ብቻ ጸጋህን ስጠኝ
የቆሰለ ልቤን ፈውስ ቶሎ አድነኝ
የሱስ ክርስቶስ . . .

አንተ ነህ የደስታ ምንጭም ህይወት አንት ነህ
በሰማይና በምድር ሌላ የለኝም
የሱስ ክርስቶስ . . .

አንድ ቀን በጋብቻ የግደይ ዘመድ የሆነ ሣህሌ የሚባል ሊጎበኘን መጣ፡፡ በባሕር ዳር ብዙ አመት ኖሯል፡፡ "የማማክርህ ነገር አለ" አለኝ። እኔም "ምን ልትለኝ ነው ሳህሌ?" አልኩት፡፡ ድምጹን ቀነስ አድርጎ "እዚህ ጎርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሰዎች እየዶለቱ ነው" አለ፡፡ ድምጹ ውስጥ ስጋት ይነበብ ነበር፡፡ ደንገጥ ብዬ "ምን እያሉ?" አልኩት፡፡ "አዲስ ሃይማኖት እያስፋፋ ነው ይላሉ" አለ። እኔም በልበ ሙሉነት "አዲስ ሃይማኖት አናስፋፋም፤ እኔ የመምሬ ወልደ ሰንበት የልጅ ልጅ ነኝ፤ እኔ የማምነውና የምሰብከው እንደቀድሞዎቹ እንደነ አባሰላማ ነው፤ ለማወቅ የሚፈልግ መጥቶ ያነጋግረኝ፡፡ ከዚያም በላይ እሁድ እሁድ ጠዋት እቤቴ በማደርገው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ሊሰማ ይችላል" አልኩት። ሣህሌም ፈርጠም ብሎ "የሚቃወሙት እኮ ያቺን ስብሰባ ነው፤ ከመደብደብና ከመግደልም ወደ ኋላ አይመለሱም፤ መጠንቀቅ አለብህ" አለኝ።

የፖሊቴክኒክ አስተዳዳሪውም አንድ ቀን እንደ ቀልድ አድርጎ "በትምህርት ቤት ውስጥ የሃይማኖት ስብሰባ ማድረግ እኮ አይፈቀድም" ብሎኝ ነበር፡፡ በነገሩ በመጠኑ ተነጋገርንና "ሕጉ የተጻፈው የት ነው?" አልኳቸው!! ሊያሳዩኝ ተስማምተን ተለያየን፡፡ እንዲህ የሚል የተጻፈ ሕግ ስላልነበረ አላሳዩኝም፡፡

በከተማው የአምልኮ ቦታ መፈለጌን ቀጠልሁ፤ ላገኝ እንደማልችል ስረዳ አንዲት ቻፕል ብጤ ለመሥራት ወሰኜ ቦታ መፈለግ ጀመርኹ:: በ2 ሺህ ብር 625 ካሬ ሜትር ቦታ ት/ቤታችን አጠገብ አገኘሁ። በባሕር ዳር አምልኮ መጀመሬን ቤተ ክርስቲያን ሰምታ ስለ ነበር እንደ አንድ የመሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ እንድትቆጠር ተወሰነ:: ሕንፃውን እኔ የማሠራ ከሆነ ለቦታው መግዢያ ቤተ ክርስቲያን እንድትከፍል ተወሰነ:: ከእስራቴ ባጠራቅምሁትና ጥቂት ወንድሞች (አንዱ ሚስተር ዌንገር ነበሩ) በሰጡኝ ገንዘብ አንዲት 5 ሜትር በ6 ሜትር የሆነች ቻፕል በ1956 ዓ.ም የክረምት ወራት አሠራሁ::

ቻፕሏ የተሠራችው እኔ የፖሊቴክኒክ ምክትል ዲሬክተር ሆኜ የተሾምኩበትና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አገልግሎት በተጀመረበት አመት ነበር:: በ1956 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ለአገልግሎት የሚሰማሩትን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የምደባ ሥራ የሚሰራውን ዶክተር ሰሎሞን እንቋይን አውቀው ስለ ነበር ወንጌላውያን ክርስቲያን ተማሪዎችን እንዲመድቡልን ጠየኩት:: አቁባዝጊ ሥዩምንና ብርሃኔ አብርሃን መደበልኝ። ሁለቱም በፖሊቴክኒክ ፊዚክስ አያስተማሩ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸውም ታላቅ ድጋፍ ይሰጡኝ ነበር::



ባህር ዳር ቻፕል ፊት ለፊት





በዚያው አመት ሌላው ትልቅ ድጋፍ ያደረጉልኝ ተሰፋጽዮን ደለለው፣ ካሣ አጋፋሪ፣ ታምሬ ኪያሞ የሚባሉ አዲስ ገብ ተማሪዎች ነበሩ። ተሰፋጽዮንና ካሣ ናዝሬት ኃይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል እየሠሩ የነበረውን ሥራቸውን ትተው ወደ ከፍተኛ ትምህርት እንዲመለሱ ጎትጉቼ ወደ ባሕር ዳር አስመጥቻቸው ነበር:: ከመጡ በኋላ ተሰፋጽዮን ትምህርት ቤቱን ስላልወደደው ምክንያት ፈጥሮ ለመሄድ ተነሳ:: አመለሳለሁ ብሎኝ ከሄደ በኋላ ሳይመለስ ቀረ:: ካሳ ግን ቀጠለ::

ተስፋ ለእኔ ካለው ፍቅርና አክብሮት የተነሳ አልመለስም ብሎ አልነገረኝም:: ነገር ግን ያን ጊዜ ያደረገውንና ከዘመናት በኋላ የነገረኝን ላውሳ:: ሜኖ መጻሕፍት ቤት የሚሠራው ሙሉነህ ባቾሬ የቅርብ ጓደኛው ነው፤ ሁለቱ ተመካከረው አናቱ በጠና እንደ ታመሙ፣ የእርሱም መምጣት አስፈላጊ እንደሆነ ደብዳቤ ይጽፍለታል፤ በጣም ያዘነ መስሎ ወደ ቢሮዬ መጣ:: እንዳየሁት:-

"ምነው ለምቦጭህን ዘርግተሃል?" አልኩት:: ምንም መልስ ሳይሰጠኝ

ደብዳቤውን እንዳነብ ሰጠኝ::

"ታዲያ ምን አሰብክ?" አልኩት::

"ምን ጥያቄ አለው ጋሽ ሚሊዮን፤ እናቴ በጣም ትወደኛለች፤ እኔም እወዳታለሁ" አለኝ:: እኔም "ለመሄድ ከፈለግህ ሄደህ አይተሃቸው ቶሎ ተመለስ፤ እግዚአብሔር ይፈውስልህ" ብዬ አሰናበትኩት:: እርሱም ሳያመነታ እሺ ብሎ በልቡ እየሳቀ ወደ ተማሪዎች ዲን በመሄድ የተረከበውን ሃላፊነት አውርዶ፣ እቃውን ቀርቅቦ፣ ከባሕር ዳር ወጣ::

አገልግሎቴን ከአቁባዝጊና ብርሃኔ ጋር ቀጠልሁ። አቁባዝጊ በአለማያ ኮሌጅ የወንጌላውያን ተማሪዎች ኅብረት ሙሉ ተሳታፊ ነበር:: በክርስትና ሕይወቱ ያደገ ሰው በመሆኑ የእሁድ ጠዋት የቃል ጊዜ ከእኔጋር በየተራ እናገለግል ነበር።

ከእርሱ ጋር ያስተዋወቀኝ እሸብር ነው፤ ሁለቱም የኢትዮጵያን ወንጌላውያን ተማሪዎችን በመወከል አብረው ወደ ኬንያ ሊሙሩ ሄደው ከሌሎች የአፍሪቃ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ኮንፍረንስ ተካፍለው ነበር።

## ጅምሬ ለጊዜው ተቋረጠች

በ1960 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ከፖሊቴክኒክ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አገልግሎት ተዛወርሁ። ፖሊቴክኒክ በነበርሁበት ዘመን በትንሣኤ በዓል ጊዜ የመንፈሳዊ መነቃቃት ኮንፈረንስ ማድረግ ልምዳችን ነበር። ለዚህ ፕሮግራም ከአዲስ አበባና ከጎንደር ወገኖችን እንጋብዝ ነበር። እኔ ፖሊን የለቀቅሁ እመትም የተውኳቸው ወንድሞች ልምዳችንን በመቀጠል ኮንፈረንስ አዘጋጁ። ለራሳቸው መነቃቃት ብቻ ሳይሆን ባሕር ዳርን በወንጌል መድረስ አለብን በማለት አንዲት ትንሽ ወረቀት "የግብዣ ጥሪ" የምትል አዘጋጅተው ሕዝቡን ለመጋበዝ ወሰኑ።

ወረቀትዋን በከተማዋ ልዩ ልዩ ቦታዎች አደሉ። የድፍረታቸው ብዛት ካደሉበት ቦታዎች አንዱ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነበር። የበተስኪያኗ ቄሶች ይህችን የግብዣ ወረቀት ሲያዩ በጣም ተቆጡ። "እነኚህ ፀረ ማርያሞች በጸሎት ሐሙስ ለት ሊያርዷት ያዘግጁትን መሊና ግቢአቸው እሰረው አርደው ሊያረክሱን ነው፤ ከዚች ከተማ እናጥፋቸዋለን፤ ተነሱ ድራሻቸውን እናጥፋ" ብለው ሕዝቡን ቀስቅሰው ወደ ቻፕሏ ሄዱ:: በአምልኮ ላይ ያሉትን ደበደቡ፤ ቻፕሏንም አፈረሱ፤ በዚህ ፖሊሶችም ተባበሩዋቸው፤ ጥቂት ወንድሞች ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው አሰሩ፤ ከታሰሩት አንዱ ወንድም ተጋ ሴንዴዶ ነበር፡ ተጋ ለአንድ ወር ያህል ታስሮ ተለቀቀ። የባሕር ዳር የዚያን ጊዜ ወንጌል አገልግሎትም ተቋረጠ።





## ስለ አዲሱ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ

አንድ ቀን እቁባዝጊ በFULL GOSPEL CHRISTIAN BUSINESS MEN FELLOWSHIP መጽሔት ላይ የታተመውን ዲመስ ሸኪርያን የሚባል ሰው ምስክርነት እንዳነብ ሰጠኝ:: ምስክርነቱ በጣም ግሩም በመሆኑ ማረከኝ፤ መጽሔቷ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ፣ በልሳን ስለ መናገር፣ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቀ ሰው ስብከት ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ እንደሚመጡ ብዙ ሰዎች ከህመማቸው እንደሚፈወሱ ታትታለች፤ የሰዎች ወደ ጌታ መምጣት ጉዳይ የሁልጊዜ የውይይት ርዕሳችን ስለሆነ ስለዚህ ልምምድ በይበልጥ ለማወቅ ፈለግን::

በዚያቺው መጽሔት ላይ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ትንንሽ መጻሕፍት ተዘርዝረው ነበር:: BAPTISTS AND THE FULLNESS OF THE HOLY GHOST. PRESBETIRIANS AND THE FULLNESSS OF THE H.G., METHODISTS AND THE FULLNESS OF THE H. G. ወዘተ በሚሉ ርዕስ ጉዳዮች የተዘጋጁ ነበሩ መጻሕፍቱ:: ከአሜሪካ አስመጥተን አነብብናቸው። በዚያን ዘመን "ጰንጠቆስጤአዊ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ" በኢትዮጵያ እየተጀመረ ነበር:: ጥቂት ወጣቶች በአዲስ አበባ ዶርዜ ሃይዞ አካባቢ እየተሰበሰቡ ወንጌል እንደሚሰብኩ፣ ብዙ ሰዎች ወደ ጌታም እየመጡ እንደሆነ እንሰማ ነበር። እንቅስቃሴው እየተጋጋለ ሄደ፤ "ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን" የምትባል አዲስ አገር በቀል ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ማቀዳቸውንም ሰማን::

እኔና እቁብዝጊ ወንጌል እየተሰበከ ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ በመምጣታቸው ደስ አለን ሌላ አዲስ ቤተ ክርስቲያን መጀመሩ ግን አላስደሰተንም:: እኔ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሆኔን እንደማልተው እርሱም በሉተራንነቱ እንደሚቀጥል ነገረኝ:: ወደ አሥመራ ለሥራ ተመድቦ ሲሄድ ሁሉ የኤርትራ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ነበር የተቀላቀለው:: በዚያን ጊዜ በዳንግላ የኤስ. አይ. ኤም ሚስዮናዊ የሆኑ ሚ/ር ስፒትሰር የሚባሉ ሽማግሌ ወደ ባሕር ዳር እየመጡ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምሩን ነበር:: በስከነ ትምህርታቸውም እንደሰት

ነበር:: እነኚህን መጻሕፍት እንዲያነቧቸውና አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ጠየቅናቸው:: ካነበቡ በኋላ ስለ ትምህርቱ ሰምተው እንደ ነበር አስተምህሮው ወደ ጎን ገሸሽ የማያደረግ መሆኑን ነገሩን::

እኛም በነገሩ ማሰብና መጸልይ ጀመርን:: በሐዋርያት ዘመን ይፈጸም የነበረው ድንቅ ነገሮች በእኛም ጊዜ በአገራችን እንዲፈጸም ተመኘን:: በአመቱ መጨረሻ አነአቀባዝኒ ትምህርታቸውን ስመቀጠል ወደ ዩኒቨርስቲ ሲመለሱ እኔም ወደ ናዝሬት ተዛወርኩ::

ናዝሬት እያለሁ በደብረ ዘይት ኢቫንጀሊካል ኮሌጅ በተደረገ ኮንፈረንስ እንድናገር ተጋብዤ ነበር:: በዚህ ኮንፈረንስ ላይ ብርሃኔም ተሳትፎ ነበር:: ብርሃኔ ወደ እዚያ የመጣው በክረምቱ ጊዜ አዋሳ ላይ የተደርገውን የፔንቴኮስታሎች ስብሰባ ላይ ከተካፈለ በኋላ ነበር::

"በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቄ መጣሁ፣ አንተም መጠመቅ አለብህ" አለኝ፤

"በል እስቲ ንገረኝ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስመጠመቅ እንዴት? ምን ማድረግ ነው ያለብኝ" ብዬ ጠየቅኹት - በጉጉት ጭምር::

"ማታ እነግርሃለሁ" አለኝ:: ተናጋሪ ስለ ሆንኹ ለብቻዬ ከፍል ተሰጥቶኛል። ብርሃኔ ከማታው ፕሮግራም በኋላ ወደ ከፍሌ መጣ:: ቁጭ ብለን አወራን፤ ኢዮኤል 2፥28-32[a] አነበበልኝና እንንበርከክ ብሎ መብራቱን አጠፋ፤ እጁን ጭኖ በመንፈስ ቅዱስ እንድሞላ ሲጸልይልኝ ጀመረ::

"እኔ ስጸልይልህ አሜን አሜን ሃሌሉያ ሃሌሉያ በል" አለኝ:: ባዘዘኝ

መሠረት "አሜን! አሜን! አሜን፤ ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ"! አልኹ::

"ቶሎ ቶሎ፣ ቶሎ ቶሎ በለው!" አለኝ::

ያቅሜን ያህል ቶሎ ቶሎ ለማለት ሞከርኹ::

"ሃሉያ፣ ሃሉያ፣ ሃሉያ፣ ሉያ! ሉያ! ሉያ!" የምልም መሰለኝ::





ብርሃኔ እንደገና፡-

"በል ልቀቀው! ልቀቀው!"

በእውነቱ ምኑን እንደምለቀው ግራ ገባኝ:: ረጋ ብዬም፡-

"አይ ብርሃኔ! ይህ ልዩ ልሳን አይመስለኝም" አልኩት::

"ግዴለም በአንድ ቀን እኮ አይሆንም፤ እኔ የተናገርሁት በሁለተኛው

ቀን ነው" አለኝ። በሚቀጥለው ቀን ደገምነው፤ በልሳን አልተናገርኹም:: ይህን ዘዴ ከሌላም ሰው ጋር ናዝሬት ደገምነው፤ በልሳን አልተናገርኹም::

በበዓለ ሃምሳው ቀን ደቀመዛሙርት የሚናገሩትን ባያውቁትም ቅሉ ሰዎች በቋንቋቸን ሲናገሩ ሰምተናቸዋል ብለዋል፤ ሰው ካልሰማው ከእግዚአብሔር ጋር ንግግር መሆን አለበት ባይ ነኝ። ከዘመናት በኋላ ስለዚህ ጉዳይ ስንወያይ ወንድሜ ነጋሽ ከበደ "ይህ ነገር ለኔና ላንተ አይደለም" ያለኝን አስታውሳለሁ፡ ፡ስንመለከተው በልሳን የሚናገሩት ወይም ተናገርን የሚሉት፣ ከአኛ በኋላ ወደ ጌታ የመጡ ናቸው። "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን በየዋህነት ያልተቀበላት ሰው አይገባባትም" (ሉቃስ 18፥17) የሚለው ይመለከትን ይሆን? የዋህነት ጎድሎኝ ይሆን?" እያልሁ እስቤአለሁ፣ አሁንም አስባለሁ።

## ጥቂት ነጥቦች - በልሳን ስለ መናገር

የትውስታ ትረካዬን ቆም ሳድርግና ስለልሣን መናገር ትንሽ ልበል፤ በልሣን ስለ መናገር ብዙ መጻሕፍት አንብቤአለሁ:: ሁሉም በእስም ዙሪያ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ አይስማሙም:: ለምሳሌ ብዙ መጻሕፍት የጻፈው ጆን ማካርተር (John MaCarther) የሚባለው ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ በጴንጠቆስጤዎች ትምህርት አይስማም:: በልዩ ልሣን ስለመናገር ሲጽፍ "ያ ልሳን ሊሳው በጉባዔ መካከል ያለ ሰው የሚናገረው መሆን አለበት" ይላል:: በዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ስሁለት ተከፍላለች::

ስለ ልሳን መጀመሪያ ያነበብሁት They Spoke in Other Tongues የሚባለውን በጆን ሼሪል (John Sherill) የተጻፈውን ነው:: ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ከብዙዎች ጋር ተነጋግሬአለሁ:: በልሳን እንናገራለን የሚሉት ቀስ ብሎ ይመጣል ከማለት ዉጭ ብዙም አይተርኩም ወይም አይከራከሩም::

ስለዚህ ጉዳይ ሰፊ ውይይት ያደረኩት ከቅርብ ወዳጄ ከማሞ ገ/መስቀል ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ገልጠን አጥንተናል፤ ስለ ልሳን በብዛት የጻፈ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው:: ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ፣ ማርቆስ በ16፥17 ጠቀስ አድርገው ከማለፋቸው በቀር ሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አልጻፉም:: ጳውሎስም ቢሆን ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው የጻፈው። በአጭሩ የተረዳናቸውን ነጥቦች ብቻ ላስቀምጥ።

አንደኛ:-

ልሳን ተናጋሪው የማይገባው በሌላ አገር የሚናገሩበት ቋንቋ ነው:: ቃሉ እንደሚለው:- "መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው ችሎታ መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ . . . ይህንንም ድምጽ በሰሙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ በየቋንቋቸው ሲናገሩ ስለ ሰሙዋቸው ተደነቁ" (ሐዋ 2፥4፡6)::

ሁለተኛ:-

ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው፤ "ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አሉ፤ መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው... መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ ሰው በጥበብ የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ሰው ደግሞ ያው መንፈስ በእውቀት የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ... እንዲሁም ላንዱ በአዲስ (ባልተለመዱ) ቋንቋዎች የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ ባልተለመዱ ቋንቋዎች የተነገረውን የመተርጎም ችሎታ ይሰጠዋል፤" (1 ቆሮ. 12፥4, 8, 10):: ሁሉም ክርስቲያን በልሳን የመናገር ስጦታ እንደ ሌለው ልብ ይሏል። "ሁሉም የመፈወስ ስጦታ የላቸውም፤ ሁሉም በአዲስ ቋንቋ የመናገር ችሎታ የላቸውም፤ (1 ቆሮ. 12፥30)::





ሦስተኛ:-

በልሳን መናገር ለምእመኑ የግል ጥቅም ነው፤ "በአዲስ ቋንቋ የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ ምክንያቱም ምስጢር የሆነውን ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሚናገር የሚናገረውን ቃል የሚያውቀው የለም፤ . . በአዲስ ቋንቋ የሚናገር ሰው እራሱን ብቻ ያንጻል" (1 ቆሮ. 14፥2, 4):: አንድ አገልጋይ ለምሳሌ የማሕበር ጸሎት ሲያደርግ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በልሳን መናገር (መጸለይ) የለበትም ማለት ነው።

አራተኛ:-

አንድ ሰው በአደባባይ በልሳን ከተናገረ በሌላ ሰው መተርጎም አለበት፤ "በአዲስ ቋንቋ የሚናገሩ ቢኖሩ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በየተራ ይናገሩ፤ እነርሱ የሚናገሩትንም ሌላ ሰው ይተርጉም፤ የሚተረጉም ሰው ከሌለ ግን በአዲስ ቋንቋ የሚናገሩት በስብሰባ ላይ ዝም ይበሉ፤ ለእግዚአብሔር ብቻ ይናገሩ፤" (1 ቆሮ 14፥27-28):: እንደ እኔ ግምት በአደባባይ በልሳን የሚናገሩ መንፈሳዊነታቸውን ለመግለጽ የሚያደርጉት ይመስለኛል:: እንግዲህ እግዚአብሔር በልሳን የመናገር ስጦታ ባይሰጠኝም ሌሎች ስጦታዎች ሰጥቶኛል:: ስለ ሰጠኝ ስጦታዎቹ አመሰግነዋለሁ:: የሰጠኝን ስጦታዎች በሚገባ እንድጠቀምበት እርዳኝ እያልሁ እጸልያለሁ።